(ለህዝብ ምክክር የቀረበ ረቂቅ)

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የሚኒስትሮች ምክር ቤት

## ደንብ ቁጥር .... / ፪ሺ፲፱

# የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንትን

# ለመደንገግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

ኢትዮጵያ ግልጽ፣ በአግባቡ ቁጥጥር የሚደረግበት እና ንቁ የካፒታል ገበያ እንዲለማ ቁርጠኛ በመሆኗ፤

የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንትን ማሰባሰብ የፋይናንስ ገበያዎችን ለማነልበት፣ የገንዘብ ፍሰትን ለማሳደግ፣ በሀገር ውስጥ ቁጠባና ኢንቨስትመንት መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት እና ኢትዮጵያን ከዓለም አቀፍ የካፒታል ገበያ ስነ-ምህዳር ጋር ለማስተሳሰር ወሳኝ በመሆኑ፤

የካፒታል እና ኢንቨስትመንት ፍሰትን ከፋይናንስ መረጋጋት፣ ከኢንቨስተሮች ጥበቃ እና ከማክሮ ኢኮኖሚ ጥንቃቄ ክትትል ጋር የሚያመዛዝን ወጥ የሆነ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት የሕግ እና የቁጥጥር ማዕቀፍ መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፭ሺ፬፻፸፰/፪ሺ፲፫ አንቀጽ ፭፻፳(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ደንብ ቁጥር ..../፪ሺ፲፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

፩/ "ባለሥልጣን" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፫(፩) መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ነው፤

፪/ "ሥልጣን የተሰጠው መንዛሪ" ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዋጅ ቁጥር ፭ሺ፫፻፶፱/፪ሺ፲፯ አንቀጽ ፪(፭) የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

፫/ "ተጠቃሚ ባለቤት" ማለት ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ጋር በተያያዘ ወይም ከሰነደ ሙዓለ ንዋዮቹ ከሚመነጩ ሁሉም መብቶች፣ ጥቅሞች፣ ስልጣኖች እና ልዩ መብቶች እንዲሁም ሁሉም ኃላፊነቶች፣ ተግባራት እና ግዴታዎች ተጠቃሚ የሆነው የሰነደ ሙዓለ ንዋዩ የመጨረሻ ባለቤት ነው፤

፬/ "የጠባቂነት ውል" ማለት በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር እና በተሰየመ ጠባቂ መካከል፣ ወይም በዓለም አቀፍ ጠባቂ እና በተሰየመ ጠባቂ መካከል የሚደረግ ሆኖ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን መያዝን፣ ማስቀመጥና መጠበቅን፣ ማስተዳደርን እና መዝገብ መያዝን የሚገዛ የጽሁፍ ውል ነው፤

፭/ "የተሰየመ ጠባቂ" ማለት የጥበቃ አገልግሎት እንዲሰጥ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ጠባቂ ወይም ንዑስ ጠባቂ ነው፤

፮/ "ብቁ የውጭ ሃገር ገንዘብ" ማለት ከኢትዮጵያ ሕጋዊ የመገበያያ ገንዘብ ውጭ የሆነ በቀላሉ ሊመነዘር የሚችል ማንኛውም ገንዘብ ሆኖ፡-

ሀ) ለዓለም አቀፍ ግብይቶች ክፍያ ለመፈጸም በስፋት የሚያገለግል፤

ለ) በዋና ዋና ዓለም አቀፍ የምንዛሪ ገበያዎች ላይ ግብይት የሚደረግበት፤ እና

ሐ) በዓለም አቀፉ የገንዘብ ድርጅት እንደ የመጠባበቂያ ገንዘብ እውቅና የተሰጠው ወይም በብሔራዊ ባንክ በሚወጣ መመሪያ ለዚሁ ዓላማ በተለይ የተሰየመ ነው፤

፰/ “የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት” ማለት በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ የሚደረግ ድንበር ተሻጋሪ ኢንቨስትመንት ነው፤

፱/ “የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር” ማለት በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት የማድረግ ተግባራት ላይ የሚሳተፍ ኢንቨስተር ነው፤

፲/ “ዓለም አቀፍ ጠባቂ” ማለት የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በተለያዩ አገሮች ከሚያከናውናቸው የኢንቨስትመንት ተግባራት ጋር የተያያዙ የገንዘብ ሰነዶችን እንዲያስቀምጥና እንዲጠብቅ በወኪልነት የሾመው ከኢትዮጵያ ውጭ የተቋቋመ ጠባቂ ነው፤

፲፩/ “ደንበኛን ማወቅ” ማለት የደንበኞችን፣ የተገልጋዮችን እና የተጠቃሚ ባለቤቶችን ማንነት ለመለየት፣ ለማረጋገጥ እና ለመከታተል፣ የንግድ ግንኙነቱን ባህሪና ዓላማ ለመረዳት፣ እንዲሁም በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን እና ሌሎች የፋይናንስ ወንጀል ስጋቶችን ለመገምገም፣ ለመቆጣጠር እና ለመከላከል ተፈጻሚ በሆኑ ሕጎች እና መመዘኛዎች መሠረት የሚተገበሩ ፖሊሲዎች፣ የአሰራር ሂደቶች እና ቁጥጥሮች ናቸው፤

፲፪/ “የገበያ መሰረተ ልማቶች” ማለት የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ክፍያ ማጣራትና መፈጸም፣ ምዝገባ እና ግብይት የሚያስችሉ ስርዓቶች፣ መገልገያዎች እና ተቋማት ሆነው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያዎችን እንዲሁም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያዎችን ያካትታሉ፤

፲፫/ “ብሔራዊ ባንክ” ማለት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዋጅ ቁጥር ፭፻፫የሃ፱/፪፻፲፯ መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ነው፤

፲፫/ “የባህር ማዶ የፋይናንስ ማዕከል” ማለት በዋናነት የፋይናንስ አገልግሎቶችን የሚሰጥ እና የውጭ ካፒታልን ለመሳብ ታስበው በተዘረጉ ልዩ የታክስ አያያዝ፣ በላላ የቁጥጥር ወይም መረጃ ይፋ የማድረግ መስፈርቶች እና በፋይናንስ ምስጢራዊነት ድንጋጌዎች የሚታወቅ ከኢትዮጵያ ውጭ ያለ ሀገር ነው፤

፲፬/ “ለፖለቲካ ተጽዕኖ የተጋለጠ ሰው” ማለት በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር ፯የ፹/፪፻፭ አንቀጽ ፪(፲፭) እና በማሻሻያዎቹ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፤

፲፭/ “አዋጅ” ማለት የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፪የሣ፫/፪፻፲፫ ነው፤

፲፮/ “ንዑስ ጠባቂ” ማለት ዓለም አቀፍ ጠባቂን በመወከል ለአንድ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር የጥበቃ አገልግሎት እንዲሰጥ በባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው የተሰየመ ጠባቂ ነው፤

፲፯/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም የሕግ ሰውነት ያለው ሰው ነው፤

፲፰/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተቀመጠ አገላለጽ የሴትንም ጾታ ይጨምራል፤

፲፱/ በአዋጁ ውስጥ ትርጉም የተሰጣቸው ማናቸውም ቃላት እና አገላለጾች በዚህ ደንብ ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡ ፡

**፫. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚከናወኑ ሁሉም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የብቁነት መስፈርቶች፣ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች መደቦች እና የምዝገባ ሂደት

### ፬. የብቁነት መስፈርቶች

፩/ ማንኛውም ሰው ከሚከተሉት አንዱ ከሆነ እንደ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ኢንቨስት ለማድረግ ብቁ ይሆናል፡-

ሀ) የውጭ ሀገር ዜጋ፤

ለ) የውጭ ሀገር ዜጋ የባለቤትነት ድርሻ የያዘበት ድርጅት፤

ሐ) ከኢትዮጵያ ውጭ በማንኛውም ኢንቨስተር የተመዘገበ ድርጅት፤

መ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ) እና (ሐ) ከተጠቀሱት ኢንቨስተሮች በሁለቱ ወይም በሦስቱ በጋራ የተቋቋመ ድርጅት፤ ወይም

ሠ) እንደ የውጭ ሀገር ኢንቨስተር መስተናገድ የመረጠ በቋሚነት በውጭ ሀገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፣ እንደ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መስተናገድ የሚፈልግ ትውልደ ኢትዮጵያዊ የውጭ ሀገር ዜጋ እንደ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ኢንቨስት ለማድረግ ብቁ አይሆንም፡ ፡

፫/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንቱ በዋናነት ከኢትዮጵያ ነዋሪዎች እንዲሁም እንደ ሀገር ውስጥ ኢንቨስተር መቆጠርን ከመረጡ ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ወይም የውጭ ሀገር ዜጎች ከሚመነጭ ማንኛውም ዓይነት የገንዘብ ኢንቨስትመንት ማስተላለፊያ ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ አይመዘገብም፤ ወይም ነባር ምዝገባው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

፬/ ሁሉም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንቶች ከኢትዮጵያ ውጭ ከሚገኙ ምንጮች ብቻ በብቁ የውጭ ሀገር ገንዘብ የሚከናወኑ ሆነው ብሔራዊ ባንክ በሚደነግገው አሰራር መሠረት ፈቃድ ባላቸው የባንክ መስመሮች በኩል መተላለፍ አለባቸው፡፡

፭/ የተሰየሙ ጠባቂዎች በብሔራዊ ባንኩ እና በባለሥልጣኑ የሚደነገጉ ሁሉንም የሪፖርት አቀራረብ፣ የክትትል እና የመዝገብ አያያዝ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡፡

፮/ ብቁ የሆነ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በዚህ ደንብ ሰንጠረዥ “ሀ” ላይ የተደነገጉትን የብቁና ተገቢነት መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱት የብቁነት መስፈርቶች ከተሟሉ በኋላ አመልካቹ በአንቀጽ ፭ መሠረት በመደብ ፭ ወይም በመደብ ፪ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተርነት ይመደባል፤ ይህ ምደባም በዚህ ደንብ መሠረት ተፈጻሚ የሚሆኑትን የቁጥጥር መስፈርቶች ይወስናል፡፡

### ፭. የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች መደቦች

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች በሁለት መደቦች መከፈል አለባቸው፡-

ሀ) የመደብ ፭ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

(፩) መንግስት፣ ብዝሃ ወገን ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም ማዕከላዊ ባንኮችን፣ መንግስታዊ የኢንቨስትመንት ፈንዶችን እና በእነዚህ ኢንቨስተሮች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ባለቤትነት የተያዙ ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ተቋማት ጨምሮ ከመንግስት ጋር የተያያዙ ኢንቨስተሮች፤

(፪) በሚገኙባቸው አገሮች ቁጥጥር የሚደረግባቸው የጡረታ እና የማህበራዊ ዋስትና ፈንዶች እንዲሁም የበጎ አድራጎት ቋሚ ፈንዶች፤

(፫) እንደ ባንኮች፣ የመድን ኩባንያዎች፣ የሀብት አስተዳዳሪዎች፣ የኢንቨስትመንት ፈንዶች፣ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች እና ሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ያሉ ተቋማዊ ኢንቨስተሮች፡፡

ለ) የመደብ ፪ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች የመደብ ፩ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተርነት ብቁነትን የማያሟሉ ሌሎች ሁሉንም ብቁ ኢንቨስተሮች ያካትታሉ፤ እነዚህም፡-

(፩) ፋውንዴሽኖች፣ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች፣ ኩባንያዎች፣ የቤተሰብ ንግዶች እና ግለሰቦች፤

(፪) ባለሥልጣኑ በሚወስናቸው ሁኔታዎች መሠረት ደንበኞችን በመወከል ኢንቨስት የሚያደርጉ ተቋማት፤

(፫) ተፈጻሚ የሆኑ የኢንቨስተር ጥበቃ መስፈርቶችን በማሟላት የሚሳተፉ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆኑ ግለሰብ መደበኛ ኢንቨስተሮች፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ የስጋት ደረጃ፣ የኢንቨስትመንት ወሰንን እንዲሁም በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል ጉዳዮችን ከግምት በማስገባት ለእያንዳንዱ መደብ ተጨማሪ ንዑስ መደቦችን እና ሁኔታዎችን ከጊዜ ወደ ጊዜ በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

**፮. በተሰየመ ጠባቂ በኩል ኢንቨስት የማድረግ ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ከኢንቨስትመንቱ ጋር የተያያዙ ሁሉም ሀብቶች እና የገንዘብ ሰነዶች በተሰየመ ጠባቂ ካልተጠበቁ በስተቀር የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በኢትዮጵያ ውስጥ በወጡ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት ማድረግ አይችልም፡፡

**፯. የማመልከቻ መስፈርቶች**

፩/ የመደብ ፩ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ለተሰየመው ጠባቂ የሚከተሉትን ማቅረብ አለባቸው፡-

ሀ) የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ፣ የሽርክና ስምምነቶች፣ የአደራ ውሎች ወይም አቻ የሆኑ የማቋቋሚያ ሰነዶችን ጨምሮ የመቋቋሚያ ሰነዶች፤ እና

ለ) የመቋቋሚያ የምስክር ወረቀቶች፣ የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀቶች ወይም ፈቃዶች፣ ወይም ኢንቨስተሩ በሚገኝበት ሀገር በሚመለከተው አካል የተሰጡ ሌሎች መደበኛ ሰነዶችን ጨምሮ ሕጋዊ ሕልውናን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡፡

፪/ የመደብ ፪ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ለተሰየመው ጠባቂ የሚከተሉትን ማቅረብ አለባቸው፡-

ሀ) የተረጋገጡ የማንነት መገለጫ ሰነዶች፤

ለ) የታክስ ከፋይነት የምስክር ወረቀት ወይም አቻ የሆነ ሰነድ፤

ሐ) የተጠቃሚ ባለቤትነት መግለጫዎች እና የባለቤትነት አደረጃጀቶች፤

መ) የገንዘብ ምንጭ ማስረጃ፤

ሠ) የፖለቲካ ተጽዕኖ የተጋለጡ ሰዎች ማጣሪያ ውጤቶች፤ እና

ረ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩን የብቁና ተገቢነት መስፈርቶች ለማረጋገጥ በተሰየመው ጠባቂ ወይም በባለሥልጣኑ የሚጠየቁ ሌሎች ማናቸውም ሰነዶች፤

፫/ ሁሉም የመደብ ፩ እና የመደብ ፪ ኢንቨስተሮች የሚከተሉትን ጨምሮ አጠቃላይ የተጠቃሚ ባለቤትነት መረጃ ማቅረብ አለባቸው፡-

ሀ) ከአመልካቹ ጀምሮ እስከ ተጠቃሚ ባለቤት(ቶች) ድረስ ያለው ሙሉ የባለቤትነት መዋቅር፤

ለ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመጨረሻ ቁጥጥር የሚያደርጉ ማናቸውንም ሰዎች ወይም ተቋማት ጨምሮ የቁጥጥር ትስስር ዝርዝር፤ እና

ሐ) ተፈጻሚ በሚሆንበት ጊዜ በባለቤትነት ወይም በቁጥጥር መዋቅሩ ውስጥ የሚገኙ ለፖለቲካ ተፅዕኖ የተጋለጡ ሰዎችን ዝርዝር።

፬/ ሁሉም ኢንቨስተሮች ባለሥልጣኑ ባጸደቀው ቅጽ መሠረት የሚከተሉትን የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማረጋገጫ ማቅረብ አለባቸው፡-

ሀ) ተፈጻሚ በሆነ ማንኛውም ዓለም አቀፍ ወይም አገራዊ ማዕቀብ ስር አለመሆናቸውን፤ እና

ለ) በሚገኙበት ሀገር ያሉትን እና በኢትዮጵያ እውቅና የተሰጣቸውን ዓለም አቀፍ መመዘኛዎች ጨምሮ ተፈጻሚ የሆኑ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል ሕጎችን እና መመዘኛዎችን ሙሉ በሙሉ ማሟላታቸውን፡፡

**፷. በተሰየመው ጠባቂ የሚደረግ የማመልከቻ ግምገማ**

፩/ የተሰየመው ጠባቂ ማመልከቻ እንደደረሰው፡-

ሀ) ተፈጻሚ የሆኑ ሕጎችን እና መመሪያዎችን በመጠቀም ደንበኛን የማወቅ ማረጋገጫ እንዲሁም በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል ማጣሪያ ያካሂዳል፤ የቀረበውን መረጃ ትክክለኛነት፣ ተአማኒነት እና በቂነት ይገመግማል፤

ለ) የዚህን ደንብ እና ሌሎች ተፈጻሚ ሕጎችን የብቁነት እና የሰነድ መስፈርቶች መሟላታቸውን ያረጋግጣል፤ እና

ሐ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ መረጃ ወይም ማብራሪያ ይጠይቃል፤ እና

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፣ ኢትዮጵያ የኢንቨስትመንት ስምምነት ወይም መደበኛ የሁለትዮሽ፣ የብዝሃ ወገን ወይም የቀጣናዊ የትብብር ዝግጅት ባላት ሀገር ውስጥ የሚገኙ፣ ከባለሥልጣኑ ጋር የቁጥጥር ትብብር እና የመረጃ ልውውጥ ያላቸው፣ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ ውጤታማ የቁጥጥር እና የማስፈጸም ትብብር የሚያረጋግጡ እንዲሁም ቢያንስ በኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጻሚ ከሆኑት የደንበኛን የማወቅ ደንቦችን እና በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን እና የፋይናንስ ወንጀል ስጋቶችን የመከላከል ደንቦችን እና ማዕቀፎችን የተቀበሉ የመደብ ፭ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ቀለል ያለ የተገቢነት ቁመና ጥናት ሊስተናገዱ ይችላሉ፡፡

፫/ የተሰየመው ጠባቂ በመደብ ፭ የተመደቡ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን የተሟላ ማመልከቻ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት አምስት (፭) የስራ ቀናት ውስጥ ማጽደቅ ወይም ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

፬/ የተሰየመው ጠባቂ በመደብ ፮ የተመደቡ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን የተሟላ ማመልከቻ ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት አስር (፲) የስራ ቀናት ውስጥ ማጽደቅ ወይም ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

፭/ የተሰየመው ጠባቂ ማንኛውንም ማመልከቻ ውድቅ ሲያደርግ፣ ገቢያውን ወይም የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ አስቸኳይ እርምጃ መውሰድ የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር፣ ጉድለቶቹን ለማረም ለአመልካቹ ምክንያታዊ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

፮/ ማመልከቻው ከጸደቀ በኋላ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ እና የተሰየመው ጠባቂ የጠባቂነት ውል መዋዋል አለባቸው።

**፷፩. ሂሳብ መክፈት እና ምዝገባ**

፩/ የጠባቂነት ውሉ እንደቀረበ፣ የተሰየመው ጠባቂ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፶፪ መሠረት የሚያስፈልጉትን ሂሳቦች የመክፈት እና የማንቀሳቀስ ስራ ማመቻቸት አለበት።

፪/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር እንደተመዘገበ የሚቆጠረው የተሰየመው ጠባቂ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሳብ ሲከፍትለት ብቻ ነው፡፡

፫/ የተሰየመው ጠባቂ እያንዳንዱን ምዝገባ ከጥበቃ ስምምነቱ ወይም ምዝገባውን ውድቅ የማድረግ ውሳኔውን ከአጭር መግለጫ ጋር ባለሥልጣኑ በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረት በአምስት (፭) የስራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት ማድረግ አለበት፡፡

**፲. የተሰየመው ጠባቂ የምዝገባ ማመልከቻን ለባለስልጣኑ ስለሚያስተላፍበት ሁኔታ**

የተሰየመው ጠባቂ የአመልካቹ የባለቤትነት፣ የአስተዳደር ወይም የቁጥጥር አደረጃጀት የተጠቃሚ ባለቤቱን በግልጽ ለመለየት የሚያስተጓጉሉ በርካታ የባለቤትነት እርከኖችን፣ የወኪል ተቋማትን፣ አደራ ጠባቂ ድርጅቶችን ወይም አገናኝ ተቋማትን የሚያካትት ሲሆን ማመልከቻውን በቀጥታ እንዲገመግመው ለባለሥልጣኑ ማስተላለፍ አለበት፡፡

**፲፩. በባለሥልጣኑ የሚደረግ ግምገማ**

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ መሠረት የተላለፈ ማመልከቻ እንደደረሰው በሦላሳ (፴) ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ገምግሞ፤ የተሰየመው ጠባቂ፡-

ሀ) አመልካቹን እንዲመዘግብ መፍቀድ፣ ወይም

ለ) ማመልከቻውን ውድቅ እንዲያደርግ በጽሁፍ ምክንያቱን በመግለጽ ማዘዝ፣

አለበት።

፪/ ባለሥልጣኑ የተጠናከረ የተገቢነት ቁመና ጥናት ለማካሄድ ተጨማሪ መረጃ ወይም ሰነዶች ሲጠይቅ ወይም ማብራሪያ ሲፈልግ፣ የተጠየቁት መስፈርቶች በአግባቡ እስኪሟሉ ድረስ የግምገማ ሂደቱ ተቋርጦ ይቆያል።

**፲፪. በተሰየመው ጠባቂ የሚደረግ ማመልከቻን ውድቅ የማድረግ ውሳኔ**

፩/ ማመልከቻው ያልተሟላ፣ ትክክል ያልሆነ፣ አሳሳች ሲሆን ወይም በሌላ መልኩ በዚህ ደንብ ወይም በሌሎች ተፈጻሚነት ባለቸው የኢትዮጵያ ሕጎች የተደነገጉትን የብቁነት፣ የብቁና ተገቢነት ወይም የህግ ተገዥነት መስፈርቶችን የማያሟላ ሲሆን፣ የተሰየመው ጠባቂ የተለዩትን ጉድለቶች እና ምክንያቶቻቸውን በመግለጽ የምዝገባ ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉን በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ በተሰየመው ጠባቂ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውድቅ የማድረግ ውሳኔው በደረሰው በ፴ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ይግባኝ ከደረሰው በኋላ ጉዳዩን ገምግሞ በ፴ ቀናት ውስጥ የሚከተሉትን ሊወስን ይችላል፡-

ሀ) የመጀመሪያውን ውሳኔ ማጽናት፣ ማሻሻል ወይም መሻር፤

ለ) ጉዳዩን ተገቢ ናቸው ብሎ ከሚያምናቸው ትዕዛዞች ጋር ለተሰየመው ጠባቂ መልሶ መላክ፤ ወይም

ሐ) ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምነውን ሌላ ማንኛውንም ትእዛዝ መስጠት፡፡

**፲፫. በባለሥልጣኑ የሚደረግ ማመልከቻን ውድቅ የማድረግ ውሳኔ**

፩/ ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲ መሠረት በተሰየመ ጠባቂ የተላለፈለትን ማመልከቻ ከገመገመ በኋላ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ምዝገባውን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፡-

ሀ) አመልካቹ፣ ተጠቃሚ ባለቤት(ቶቹ)፣ አገናኞቹ ወይም የሚገኝበት ሀገር በበቂ ሁኔታ ሊቀነሱ የማይችሉ ወሳኝ የሆነ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ የመርዳት፣ የማዕቀብ ወይም ሌሎች የፋይናንስ ወንጀል ስጋቶችን የሚያስከትሉ ሲሆን፤

ለ) አመልካቹ ከባህር ማዶ የፋይናንስ ማዕከል ወይም ከተጠናከረ የቁጥጥር ክትትል ስር ካልሆነ ሌላ ማንኛውም ሀገር ጋር ጉልህ ትስስር ያለው ሲሆን እና እነዚህ ትስስሮች በኢትዮጵያ የኢንቨስተሮች ጥበቃ፣ የገቢያ ታማኝነት ወይም የፋይናንስ መረጋጋት ላይ ስጋት የሚፈጥሩ ሲሆኑ፤

ሐ) ለባለሥልጣኑ የቀረበው መረጃ ወይም ሰነድ ሐሰተኛ፣ አሳሳች ወይም ትክክል ያልሆነ ሲሆን፤

መ) ለባለሥልጣኑ የቀረበው መረጃ ወይም ሰነድ ያልተሟላ ወይም ወሳኝ ጉድለት ያለበት ሲሆን እና ጉድለቱም በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተስተካከለ ሲሆን፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭(ለ) ዓላማ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ከባህር ማዶ የፋይናንስ ማዕከል የመነጨ ወይም ከእሱ ጋር የተገናኘ ነው የሚባለው፡-

ሀ) መኖሪያው፣ የተመዘገበ ዋና መስሪያ ቤቱ፣ የኢንቨስትመንት አስተዳዳሪው፣ ወይም ጠባቂው በእንደዚህ ዓይነት ሀገር ውስጥ ሲገኝ፤

ለ) ወሳኝ የሆነ የተጠቃሚ ባለቤትነት ድርሻው ወይም ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ በእንደዚህ ዓይነት አገሮች ውስጥ በሚገኙ ተቋማት በኩል የተያዘ ሲሆን፤ ወይም

ሐ) የኢንቨስትመንት መዋቅሩ በእንደዚህ ዓይነት አገሮች ውስጥ በሚገኙ ወይም በሚንቀሳቀሱ የኢንቨስትመንት ተቋማት ላይ የተመሰረተ ሲሆን ነው፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የገበያ ተዓማኒነትን ወይም የኢንቨስተሮችን ጥቅም ለማስጠበቅ አስቸኳይ ውድቅ የማድረግ እርምጃ የሚያስፈልግ ካልሆነ በስተቀር ጉድለቶችን ለማረም ምክንያታዊ ዕድል መስጠት አለበት፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት ማመልከቻን ውድቅ የሚያደርግበት ውሳኔ ምክንያቶቹን በመግለጽ በጽሁፍ መተላለፍ አለበት፡፡

**፲፬. የግብይት እንቅስቃሴን ስለማገድ**

፩/ ባለሥልጣኑ በራሱ አነሳሽነት ወይም በተሰየመ ጠባቂው ጥቆማ መሠረት የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ የሚከተሉትን ሲፈጽም የኢንቨስተሩን የግብይት እንቅስቃሴ በሙሉ ወይም በከፊል ሊያግድ ይችላል፡-

ሀ) የሚጠየቁ ሪፖርቶችን፣ የመረጃ ይፋ ማድረግን ፤ ወሳኝ መረጃን በዚህ ደንብ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ያላቀረበ ሲሆን፣ ወይም ለቁጥጥር ጥያቄዎች ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን፤

ለ) የብቁ እና ተገቢነትን፣ የገበያ ታማኝነትን ወይም የኢንቨስተሮችን ጥበቃ በተመለከተ ስጋት በሚፈጥር መልኩ በሀገር ውስጥ ወይም በውጭ ሀገር ባለው ተገቢ ስልጣን ባለው አካል ምርመራ እየተደረገበት ሲሆን፤

ሐ) በገበያ ታማኝነት፣ በኢንቨስተሮች ጥበቃ፣ በፋይናንስ መረጋጋት፣ በብሔራዊ ደህንነት ወይም በሕዝብ ጥቅም ላይ ስጋት የሚፈጥር ሲሆን፤

መ) የዚህን ደንብ ማንኛውንም ድንጋጌ፣ በዚህ ደንብ መሠረት የወጣ ማንኛውንም መመሪያ፣ ወይም የካፒታል ገበያን፣ የውጭ ምንዛሪን ወይም የፋይናንስ አገልግሎቶችን የሚመለከት ተፈጻሚ የሆነ ማንኛውንም የኢትዮጵያ ሕግ የጣሰ ሲሆን፡፡

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚደረግ እገዳ ለተወሰነ ጊዜ ወይም የተለዩት ጉድለቶች በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ባለው ሁኔታ እስኪታረሙ ድረስ ሊጣል ይችላል፡፡

፫/ የእገዳ ውሳኔው እና እገዳውን ለማንሳት የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች ካሉ፣ ለገበያ መሰረተ-ልማቶች በጽሁፍ መገለጽ አለባቸው፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ እገዳው ተግባራዊ ከሆነ በኋላ የእገዳውን ምክንያቶች በመግለጽ ስለ እገዳው ውሳኔ ለተሰየመው ጠባቂ ማሳወቅ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት

## የተፈቀዱ ኢንቨስትመንቶች እና ገደቦች

**፲፩. ብቁ የገንዘብ ሰነዶች**

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ኢንቨስት ማድረግ የሚችለው በሚከተሉት ሰነደ ሙሳለ ንዋዮች ላይ ብቻ ነው፡-

ሀ) የገንዘብ ገበያ ሰነዶች፤

ለ) አክሲዮኖች፤

ሐ) ብድር ሰነደ ሙሳለ ንዋዮች፤

መ) የመንግስት የብድር ሰነደ ሙሳለ ንዋዮች፤

ሠ) በባለሥልጣኑ የተመዘገቡ የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች ክፍልፋዮች ወይም አክሲዮኖች፤ እና

ረ) ተዛማጆች እና በባለሥልጣኑ ሊፈቀዱ የሚችሉ ሌሎች ሰነደ ሙሳለ ንዋዮች ወይም የገንዘብ ሰነዶች፡፡

፪/ ተፈጻሚ በሆኑ ዘርፍ-ተኮር ሕጎች የተጣሉ ገደቦችን ወይም ተገቢ ስልጣን ባለው አካል የሚሰጡ የቁጥጥር ይሁንታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ገደቦች፣ ሁኔታዎች እና የጥንቃቄ መስፈርቶች እስካሟላ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ በተመዘገበ እና በማንኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ በሚንቀሳቀስ ኩባንያ አክሲዮኖች ላይ ኢንቨስት ማድረግ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ባለው የሰነደ ሙሳለ ንዋይ ገበያ ያልተመዘገቡ ሰነደ ሙሳለ ንዋዮችን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ማናቸውንም ብቁ የገንዘብ ሰነዶች ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት ከሚከተሉት አንዱን የሚያስከትል መሆኑን ሲያረጋግጥ በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ተሳትፎ ላይ ገደቦችን፣ ሁኔታዎችን ወይም ክልከላዎችን በመመሪያ ሊጥል ይችላል፡-

ሀ) የባለሥልጣኑን እና/ወይም የብሔራዊ ባንኩን የካፒታል ገቢ እና ወጭ ፍሰቶችን ወይም ገንዘብ ወደ ውጭ ሀገር ማስተላለፍን በውጤታማነት የመከታተል፣ የመቆጣጠር ወይም በበላይነት የመምራት አቅም ሲያዳክም ወይም በከፍተኛ ሁኔታ ሲገድብ፤

ለ) በቂ ያልሆነ መረጃ ይፋ ማድረግ፣ የድርጅት አስተዳደር ጉድለቶች ወይም በቂ ባልሆነ የቁጥጥር ክትትል ምክንያት በኢንቨስተሮች ጥበቃ ላይ ስጋቶችን ሲያስከትል፤

ሐ) የባለሥልጣኑን የባለቤትነት ጣሪያዎችን፣ የተጠቃሚ ባለቤትነት መዋቅሮችን፣ የክምችት ገደቦችን ወይም የተወሰኑ የይዞታ ጊዜዎች መከበርን የመከታተል አቅም ሲያዳክም፤

መ) በፋይናንስ መረጋጋት፣ በገበያ ተዓማኒነት ወይም በካፒታል ገበያው ስርዓታዊ ዕድገት ላይ ተጨባጭ ወይም ሊከሰት የሚችል መዋቅራዊ አደጋ ስጋት ሲፈጥር፤

ሠ) ተፈጻሚነት ያላቸውን ሕጎችን የሚጥስ ሲሆን፡፡

**፲፪. በአክሲዮን ኢንቨስትመንት ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ የኢንቨስትመንት ገደቦች**

፩/ ተፈጻሚነት ባለው ሕግ ወይም በሰነደ ሙሳለ ንዋይ አውጪው የመጀመሪያ ደረጃ ተቆጣጣሪ ከፍ ያለ ይዞታ ካልተፈቀደ በስተቀር፣ ማንኛውም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር፣ ቅርበት ያላቸው ኩባንያዎቹን እና በመቀናጀት የሚንቀሳቀሱ ማናቸውንም ሰዎች ጨምሮ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከአውጪው አጠቃላይ የተከፈለ ካፒታል ከአስር በመቶ (፲%) በላይ መያዝ አይችልም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ የመደብ ፩ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች የባለሥልጣኑን ቅድመ ይሁንታ በማግኘት ከሰነደ ሙሳለ ንዋይ አውጪው የተከፈለ ካፒታል እስከ አስራ አምስት በመቶ (፲፭ %) ድረስ ሊይዙ ይችላሉ፡፡

፫/ ይዞታው ከአስር በመቶ (፲ %) ጣሪያ በላይ የሚያስከትል ማንኛውም ግዥ፡-

ሀ) የባለሥልጣኑን አስገዳጅ ይሁንታ የሚጠይቅ ይሆናል፤ ወይም

ለ) በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፫/፪፻፲፪፣ በተያያዥ ሕጎቹ እና በማሻሻያዎቹ የተደነገጉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) እና (፪) የተደነገገው ቢኖርም፣ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ ከአቅሙ በላይ በሆኑና ከሚከተሉት ሳይወሰኑ በሚፈጠሩ ምክንያቶች ከከፍተኛው ጣሪያ በላይ የያዘ እንደሆነ፡-

ሀ) የካፒታል መልሶ ማዋቀር፤

ለ) ውህደት እና ግዥ፤ ወይም

ሐ)በአውጪው የተወሰዱ ሌሎች የኩባንያ እርምጃዎች፤

ጥሰቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በአምስት (፭) የስራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ እና ለተሰየመው ጠባቂ ማሳወቅ አለበት፤ እንዲሁም ጥሰቱ ከተከሰተበት ቀን ጀምሮ በአስራ አምስት (፲፭) የስራ ቀናት ውስጥ ይዞታውን ወደ አስር በመቶ (፲%) ወይም ከዚያ በታች ለመመለስ የሚያስፈልገውን ያህል ሰነደ ሙዓለ ንዋይ መሸጥ ወይም ማስተላለፍ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው ቢኖርም፣ ባለሥልጣኑ ምክንያቱ ተገልጾ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት እና በገበያ ሁኔታዎች ወይም በገንዘብ አከልነት እጥረት ምክንያት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ከሠላሳ (፴) የስራ ቀናት ያልበለጠ የአንድ ጊዜ የጊዜ ማራዘሚያ ሊሰጥ ይችላል፡፡

፮/ ተፈጻሚነት ባለው የኢትዮጵያ ሕግ የተጣለ ማንኛውንም ገደብ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአንድ የተመዘገበ ኩባንያ ውስጥ የሁሉም የተመዘገቡ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች አጠቃላይ ጥምር የአክሲዮን ይዞታ በተወሰኑ አውጪዎች፣ ዘርፎች ወይም የሰነድ መደቦች ላይ በባለሥልጣኑ ከፍ ያለ ገደብ ካልተፈቀደ በስተቀር ከኩባንያው አጠቃላይ የአክሲዮን ካፒታል ከሠላሳ በመቶ (፴%) መብለጥ የለበትም።

፯/ የገበያ መሰረተ-ልማቶች የኢንቨስትመንት ገደቦቹ እንደተደረሱ መከታተል እና ተጨማሪ የውጭ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግዥዎችን ማገድ አለባቸው፡፡

፰/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ኢንቨስት ባደረገበት አውጪ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል መሆን ወይም በአስተዳደራዊ ተግባራት መሳተፍ የለበትም፤ ማንኛውም እንደዚህ ዓይነት ድርጊትም ቁጥጥር የማድረግ ፍላጎት ማሰረጃ ሆኖ የሚቆጠር ሲሆን በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፭፻፷፫/፪፻፲፪ ወይም በማሻሻያዎቹ መሠረት ኢንቨስትመንቱ እንደ የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ዳግም እንዲመደብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፱/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) ዓላማ በጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ መስጠትን፣ የባለአክሲዮን ሀሳቦችን ማቅረብን እና ሌሎች ተመሳሳይ የኩባንያ እርምጃዎችን ጨምሮ መደበኛ የባለአክሲዮን መብቶችን መጠቀም በአስተዳደራዊ ተግባራት ውስጥ እንደ መሳተፍ አይቆጠርም፡፡ በአስተዳደራዊ ተግባራት ውስጥ መሳተፍ ተከናውኗል የሚባለው የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፡-

ሀ) በዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ የድምጽ መስጫ መብት ያለው መቀመጫ ሲይዝ፤

ለ) የዕለት ተዕለት የስራ ክንውን ወይም የአስፈጻሚነት ስልጣን ሲጠቀም፤ ወይም

ሐ) በዋና ዋና የንግድ ውሳኔዎችን የማገድ መብት ወይም የአስፈጻሚ ኃላፊዎችን የመሾም መብት የሚሰጥ ስምምነት ሲፈጽም ብቻ ነው፡፡

## ክፍል አራት

## ስልጣንና ተግባራት እና የተቋማት ቅንጅት ማዕቀፎች

### ፲፯. የባለሥልጣኑ ስልጣን እና ተግባራት

፩/ ባለሥልጣኑ የካፒታል ገበያውን ለመቆጣጠር፣ ለመከታተል እና በበላይነት ለመምራት በአዋጁ አንቀጽ ፮ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ለዚህ ደንብ ዓላማ፡-

ሀ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን ምዝገባ እና ምደባ በተመለከተ ማስታወቂያዎችን ወይም ጋይድላይኖችን ያወጣል፤ እንዲሁም ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች አገልግሎት ለሚያመቻቹ ወይም ለሚሰጡ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና የገበያ መሰረተ-ልማቶች የተለዩ የፈቃድ አሰጣጥ፣ የስራ ስነ-ምግባር እና የጥንቃቄ መስፈርቶችን ያወጣል እንዲሁም ያስፈጽማል፤

ለ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ግብይቶች በአግባቡ፣ በተረጋጋ እና በቀልጣፋ ሁኔታ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ እና አጠቃላይ የገበያ ተዓማኒነትን ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑ የግብይት ደንቦችን፣ የክፍያ አፈጻጸም ስርዓቶችን እና የአሰራር ጥንቃቄዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ የገበያ መሰረተ-ልማቶችን ያዛል፤

ሐ) ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ተግባራት የሚመነጩ መዋቅራዊ እና የገበያ መረጋጋት ስጋቶችን ለመለየት፣ ለመከታተል እና ለመቀነስ የሚረዱ የጥንቃቄ እርምጃዎችን ያወጣል እንዲሁም ተግባራዊ ያደርጋል፤ እና

መ) የተመዘበሩ ሃብቶችን የመለየት፣ የመከታተል፣ የማገድ እና የማስመለስ ስልጣንን እንዲሁም በማስፈጸም ተግባራቱ የጥቆማ መረጃዎችን የመጠቀም ስልጣንን ጨምሮ ለኢንቨስተሮች ሀብት ጥበቃ እና ለሕግ ማስከበር የሚያገለግሉ ስርዓቶችን ይዘረጋል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ ተፈጻሚነት ባላቸው የምስጢራዊነት፣ የግል መረጃ ጥበቃ እና የሳይበር ደህንነት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ባለስልጣኑ በገበያ መሰረተ-ልማቶች፣ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና በብሔራዊ ባንክ ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ተቋማት መካከል የሥርዓት መናበብን እና ውጤታማ የመረጃ ልውውጥን የሚያረጋግጡ አደረጃጀቶችን ሊዘረጋ ይችላል፡፡

### ፲፰. የብሔራዊ ባንክ ስልጣን እና ተግባራት

፩/ ብሔራዊ ባንክ፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፱/፪ሺ፲፯ አንቀጽ ፮ በተሰጠው ስልጣን መሠረት የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንትን ማክሮ-ፋይናንስ እና ከውጭ ምንዛሪ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የመቆጣጠር ኃላፊነት አለበት፤ በተለይም፡-

ሀ) የገቢ እና ወጭ ፍሰቶችን ጨምሮ ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት የሚመነጩ ድንበር ተሻጋሪ የካፒታል ፍሰቶችን ይቆጣጠራል እንዲሁም ገቢዎችን ወደ ውጭ ሀገር ማዛወርን ይፈቅዳል፤

ለ) ከፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር የተያያዘ የውጭ ምንዛሪ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባበትን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመነዘርበትን፣ የሚያዝበትን ወይም ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ የሚዛወርበትን ሁኔታዎች ይወስናል፤

ሐ) በገበያ ጫና፣ በከፍተኛ መዋዠቅ ወይም በድንገተኛ የካፒታል ፍሰት መቀልበስ ወቅቶች የሚሰጡ ምላሾችን ይከታተላል እንዲሁም ያስተባብራል፤ እና

መ) ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ የውጭ ምንዛሪን በተመለከተ ባንኮችን እና ሥልጣን የተሰጣቸውን መንዛሪዎች ይቆጣጠራል፡፡

### ፲፱. የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት የተማከለ ሪፖርት አቀራረብ እና ክትትል

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች የሚከናወኑት እና ክትትል የሚደረግባቸው ፈቃድ ባላቸው የገበያ መሰረተ-ልማቶች እና የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች አማካኝነት መሆን አለበት፡፡

፪/ በሕግ የተጣሉበት ሌሎች ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት፡-

ሀ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን የተመለከተ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ባለቤትነት ትክክለኛ እና ወቅታዊ መዝገብ ይይዛል፤

ለ) ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንቶች ጋር የተያያዙ የግብይት፣ የይዞታ እና የኩባንያ እርምጃ መረጃዎችን ይሰበስባል፤

ሐ) ተገቢውን የኢንቨስተር መለያ፣ እና የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ይዞታዎችን መለየት ያረጋግጣል፤ እና

መ) ለባለሥልጣኑ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች በቀጥታ፣ በአስተማማኝ እና በወቅቱ የማግኘት ዕድል ይሰጣል።

፫/ በብሔራዊ ባንኩ ፈቃድ የተሰጣቸው ባንኮች እና ሥልጣን የተሰጣቸው መንዛሪዎች ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት የሚመነጩ የካፒታል ገቢ ፍሰቶችን እና ገቢዎችን ወደ ውጭ ሀገር ማዛወርን በውጭ ምንዛሪ ሕጎች እና በብሔራዊ ባንክ በሚወጡ መመሪያዎች መሠረት ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

**፳፯. የማስተባበሪያ ኮሚቴን ስለማቋቋም**

፩/ ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ የመንግስት ተግባራትን ለማስተባበር እና የመረጃ ልውውጥን ለማመቻቸት ኮሚቴ ሊቋቋም ይችላል።

፪/ ባለሥልጣኑ ወይም ብሔራዊ ባንክ ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር የኮሚቴውን ማቋቋም ሊያስጀምሩ እና ሊያስተባብሩ ይችላሉ።

፫/ ኮሚቴው ለተቋቋመበት የተለየ ዓላማ በመመርኮዝ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ሊቋቋም ይችላል።

፬/ ኮሚቴው ከሚከተሉት ተቋማት የተውጣጡ ተወካዮችን ያካትታል፡-

ሀ) የገንዘብ ሚኒስቴር፤

ለ) የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፤

ሐ) የኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ባለሥልጣን፤

መ) የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፤

ሠ) የንግድ እና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፤

ረ) የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት፤

ሰ) በኮሚቴው አባላት የሚወሰኑ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ተቋማት።

፭/ ኮሚቴው በገንዘብ ሚኒስትሩ ወይም እርሱ በሚወክለው ተወካይ ይመራል።

፮/ ኮሚቴው፡-

ሀ) በገበያ ጫና ወቅቶች የሚሰጡ የተቀናጁ ምላሾችን ያስተባብራል፤

ለ) በተቋማት መካከል የመረጃ መጋራትን እና የመረጃ ልውውጥን ያመቻቻል፤

ሐ) ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር አግባብነት ባላቸው ፖሊሲዎች እና የሕግ ማዕቀፎች ላይ ግምገማ በማድረግ የውሳኔ ሃሳቦችን ያቀርባል፤ እና

መ) ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ተግባራት ያከናውናል።

፯/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ኮሚቴው ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ በልዩ ሁኔታ ይሰበሰባል።

## ክፍል አምስት

## የገበያ ተደራሽነት፣ ሂሳቦች እና ግብይት

**፳፩. ሂሳብ ስለመክፈት**

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ማንኛውንም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት የሚከተሉትን መክፈት እና መያዝ አለበት፡-

ሀ) በባለሥልጣኑ ይሁንታ ወይም ፈቃድ በተሰጠው ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋየች ግምጃ ቤት ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋየች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ደንቦች ወይም አሰራሮች መሠረት የተከፈተ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሳብ፤

ለ) ፈቃድ ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ የግብይት መድረክ ደንቦች መሠረት ከግብይት አባል ጋር የተከፈተ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይት ሂሳብ፤

ሐ) ፈቃድ ካለው የንግድ ባንክ የተከፈተ የውጭ ሀገር ገንዘብ የባንክ ሂሳብ እና ነዋሪ ያልሆነ የብር የባንክ ሂሳብ፤ እና

መ) በተሰየመ ጠባቂ የሚያዝ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጥበቃ ሂሳብ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን ሂሳቦች መክፈት፣ ማንቀሳቀስ እና መዝጋት በባለሥልጣኑ እና በብሔራዊ ባንክ በየቁጥጥር ተልዕኮዋቸው መሠረት በሚወጡ ተፈጻሚ ሕጎች እና አሰራሮች የሚገዛ ይሆናል፡፡

**፳፪. የሀገር ውስጥ አገልግሎት ሰጭዎችን ስለመጠቀም**

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ላይ የሚያደርጋቸው ግብይቶች በባለሥልጣኑ ፈቃድ በተሰጠው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ወይም ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ የግብይት መድረክ ላይ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች በኩል መከናወን አለባቸው፡፡

፪/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በባለሥልጣኑ እና በብሔራዊ ባንክ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚደነገጉ ሁኔታዎችን ወይም መመሪያዎችን ማሟላት አለበት፡፡

**፳፫. ክፍያ ማጣራት እና መፈጸም**

፩/ ተፈጻሚነት ያላቸው የካፒታል ፍሰት እና የይዞታ ጊዜ መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ማንኛውም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ግብይቶች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋየች ግምጃ ቤት እና/ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋየች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ በኩል፣ በደንቦቻቸው እና በአሰራሮቻቸው መሠረት፣ በተወሰነው የክፍያ መፈጸሚያ ቀን እና ርክክብን ከክፍያ ጋር የማቀናጀት እንዲሁም የክፍያ ፍጻሜነት ዝግጅቶችን ጨምሮ በተገለጸው የክፍያ አፈጻጸም ሥርዓት መሠረት ክፍያቸው መጣራት እና መፈጸም አለበት፡፡

፪/ ማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋየች ግምጃ ቤት ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋየች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የባለሥልጣኑን ይሁንታ በማግኘት የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሳቦች፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ግብይቶች እንዲሁም የግብይቶቻቸውን ክፍያ ማጣራት እና መፈጸም በተመለከተ ዝርዝር ደንቦችን እና አሰራሮችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፳፬. የጥበቃ አደረጃጀት**

፩/ በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ባለቤትነት የተያዙ ሁሉም ብቁ የገንዘብ ሰነዶች በባለሥልጣኑ ፈቃድ በተሰጠው የተሰየመ በጥበቃ ስር ሊያዙ ወይም ክትትል ለደረግባቸው ይገባል፡፡

፪/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ለሚያከናውናቸው የኢንቨስትመንት ተግባራት ጥበቃ በመወከል እንዲሰራ ዓለም አቀፍ ጠባቂ ሊሾሙ ይችላሉ፡፡

፫/ ዓለም አቀፍ ጠባቂው ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች አገልግሎት መስጠት የሚችለው በኢትዮጵያ ፈቃድ ባለው ንዑስ ጠባቂ በኩል ወይም በባለሥልጣኑ በአግባቡ ፈቃድ በተሰጠው ተቀጥላ ኩባንያ ወይም ቅርንጫፍ በኩል ብቻ ነው፡፡

፬/ የተሰየመ ጠባቂ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተርን ወይም ለአንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ለሚሰራ ዓለም አቀፍ ጠባቂ በመወከል በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት የጥቅል የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሳብ ሊይዝ ይችላል፡፡

፭/ የጥቅል ሂሳቡ በተሰየመው ጠባቂ ስም የሚከፈት፣ “ጥቅል - የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት” ተብሎ የሚሰየም ሆኖ የአንድ የተሰየመ ጠባቂ የሁሉንም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች የተጠቃለለ ይዞታ የሚወክል መሆን አለበት።

፮/ ንዑስ ጠባቂው ዓለም አቀፍ ጠባቂው የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩን በመወከል ለመስራት አስፈላጊው ውክልና እንዳለው ማረጋገጥ አለበት፡፡

፯/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ ወይም ዓለም አቀፍ ጠባቂው ማንኛውንም ኢንቨስትመንት ከማድረጉ በፊት ከተሰየመው ጠባቂ ጋር ስምምነት መፈጸም አለበት፡፡

፰/ በዓለም አቀፍ ጠባቂው እና በንዑስ ጠባቂው መካከል የሚደረገው ስምምነት እንዲጸድቅ ለባለሥልጣኑ መቅረብ አለበት፡፡

፱/ ንዑስ ጠባቂዎች ስራ መጀመር የሚችሉት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት የጠባቂነት ውሉ ከጸደቀ በኋላ ብቻ ነው፡፡

፲/ የተሰየመው ጠባቂ በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩን ወይም በዓለም አቀፍ ጠባቂውን በመወከል የሚሰራ ሲሆን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ምዝገባ፣ ማስቀመጥ እንዲሁም ክፍያ ማጣራት እና መፈጸምን በተመለከተ በባለሥልጣኑ የተቀመጡ ወይም የጸደቁ ሁሉንም ተፈጻሚነት ያላቸውን መስፈርቶች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

**፳፫. የንግድ ባንኮች በጠባቂነት ስለሚሰሩበት ሁኔታ**

፩/ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ የተሰጣቸው የንግድ ባንኮች የሚከተሉትን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች የጥበቃ አገልግሎት ሊሰጡ ይችላሉ፡-

ሀ) ባንኩ በጥሩ የቁጥጥር አቋም ላይ የሚገኝ እና የጥበቃ አገልግሎት ለመስጠት ብቁ መሆኑን የሚያረጋግጥ የተቃውሞ አልባ ደብዳቤ እና የመልካም አቋም ማረጋገጫ ከብሔራዊ ባንክ ማግኘት፤

ለ) በብሔራዊ ባንክ ለባንክ ስራ ተግባራት የተደነገገውን አነስተኛ የተከፈለ ካፒታል እና የካፒታል በቂነት ምጣኔ መጠበቅ፤

ሐ) ጠንካራ የገንዘብ አከልነት አቋም መጠበቅ እና በብሔራዊ ባንክ የተወሰኑትን ሁሉንም የገንዘብ-አከል ንብረት መስፈርቶች ማሟላት፤

መ) ተፈጻሚነት ያላቸውን የባዜል መመዘኛዎችን ወይም በብሔራዊ ባንክ የወጡ ሌሎች የጥንቃቄ መመዘኛዎችን እና መመሪያዎችን በወሳኝ ሁኔታ ያለማክበር ወይም ያልታረሙ ጥሰቶች መዝገብ አለመኖር፤

ሠ) የሚከተሉትን ለማከናወን የሚያስፈልጉ የቴክኖሎጂ መሰረተ-ልማቶች፣ ስርዓቶች እና ውስጣዊ ቁጥጥሮች መኖር፡-

(፩) በጥበቃ ስር የተያዙ ሀብቶችን ማስቀመጥና መጠበቅ፤ እና

(፪) በባንኩ የራሱ ሀብቶች እና በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ስም በሚያዙ ሀብቶች መካከል ጥብቅ የሆነ የተግባር፣ የአሰራር እና የሕግ መለያየትን ማረጋገጥ፡፡

ረ) የሚከተሉትን የሚያከናውን ለጥበቃ ስራዎች ብቻ የተመደበ የተለየ እና የተከለለ የስራ ክፍል ማቋቋም እና መያዝ፡-

(፩) ከባንኩ የንግድ ባንክ ስራ ተግባራት ተነጥሎ መስራት፤

(፪) የጥቅም ግጭቶችን ለመከላከል የሚያስችሉ የሪፖርት አቀራረብ መስመሮችን እና ውስጣዊ ቁጥጥር ማዕቀፎችን መያዝ፤

(፫) ትክክለኛ የተጠቃሚ ባለቤትነት መዝገቦችን መያዝን ጨምሮ ጠንካራ የደንበኛ ሀብት ጥበቃ፣ የሂሳብ ማስታረቅ እና የመዝገብ አያያዝ ሂደቶችን መተግበር፤

(፬) ምስጢራዊ የደንበኛ መረጃን ለመጠበቅ የመረጃ መከለያዎችን እና የተደራሽነት ቁጥጥሮችን ማቋቋም፤ እና

(፭) ለጥበቃ ስራዎች የተለዩ የስራ ቀጣይነት እና ከአደጋ የማገገም ዝግጅቶችን መያዝ፡፡

ሰ) በባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊደነገጉ የሚችሉ ሌሎች መስፈርቶችን ማሟላት፡፡

፪/ የጥበቃ አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ባንክ ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች በጥበቃ ስር የተያዙ ገንዘቦችን የራሱን ወይም የሌሎች ደንበኞቹን የባንክ ስራ ተግባራት ለመደገፍ፣ ለመደጎም ወይም ከእነሱ ጋር ለመቀላቀል መጠቀም አይችልም።

፫/ በጥበቃ ስራዎች ላይ የሚደረጉ የቁጥጥር እና የኦዲት ተግባራት ተጨባጭ ክትትል እና የሕግ ማክበርን ለማረጋገጥ ከባንኩ የንግድ አመራር እና የሪፖርት አቀራረብ መዋቅሮች ነጻ መሆን አለባቸው፡፡

፬/ የጥበቃ አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ባንክ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን መረጃዎች፣ ወይም መዝገቦች ለንግድ ባንክ ስራዎቹ፣ ለማስታወቂያ ወይም ከጥበቃ አገልግሎት ጋር ላልተያያዙ ሌሎች ተግባራት መጠቀም አይችልም፡፡

፭/ ከላይ የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው የጥበቃ አገልግሎት ለመስጠት የሚፈልግ የንግድ ባንክ በባለሥልጣኑ አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች የተደነገጉትን የፈቃድ አሰጣጥ እና ቀጣይ መስፈርቶች በማሟላት ከባለሥልጣኑ ተፈጻሚ የሆነውን ፈቃድ ማመልከት እና ማግኘት አለበት፡፡

**<u>፳፮</u>. የተሰየመ ጠባቂ ስለመቀየር**

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ወይም ዓለም አቀፍ ጠባቂው ለባለሥልጣኑ፣ ለማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት እና ለሚመለከታቸው ጠባቂዎች የቅድሚያ የጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት በማንኛውም ጊዜ የተሰየመውን ጠባቂ ሊቀይር ይችላል፡፡

፪/ ዓለም አቀፍ ጠባቂው የንዑስ ጠባቂ ለውጥ ለመጠየቅ ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ የጽሁፍ ውክልና ሊኖረው ይገባል፡፡

፫/ የሚቀየረው ጠባቂ ሁሉንም ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች፣ የጥሬ ገንዘብ ቀሪ ሂሳቦች እና መዝገቦች በማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት በተደነገገው የጊዜ ገደብ እና አሰራር መሠረት ለአዲሱ ጠባቂ ማስተላለፍ አለበት፡፡

፬/ ከላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የጠባቂ ፈቃድን መመለስ በተመለከተ የወጣው አግባብነት ያለው የባለሥልጣኑ መመሪያ ለጠባቂ ለውጥ ጥያቄዎችም እንደአግባብነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፭/ ከጠባቂ ለውጥ ጋር የተያያዘ ማንኛውም ሌላ ጉዳይ በባለሥልጣኑ በሚወሰኑት መስፈርቶች መሠረት የሚስተናገድ ይሆናል፡፡

**<u>፳፯</u>. የተከፈለ ካፒታልን ስለማሳደግ**

፩/ በባለሥልጣኑ ተፈጻሚነት ባላቸው መሪያዎች የተደነገጉት አነስተኛ የተከፈለ ካፒታል መስፈርቶች ቢኖሩም፣ ባለሥልጣኑ ነባሩ ዝቅተኛ የካፒታል መስፈርት የጠባቂዎችን መዋቅራዊ እና የአሰራር ስጋት ገጽታ ለመሸፈን በቂ አይደለም ብሎ ከወሰነ ለተሰየመ ጠባቂ የሚያስፈልገውን አነስተኛ የካፒታል መጠን ሊጨምር ይችላል፡፡

፪/ ባለሥልጣኑ አነስተኛውን የካፒታል መስፈርት ለመጨመር ሲወስን የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት አለበት፡-

ሀ) ውስብስብ የገንዘብ ሰነዶችን ማስቀመጥና መጠበቅን ጨምሮ የጥበቃ አገልግሎቶቹን ባህሪ፣ መጠን እና ውስብስብነት፤

ለ) የጠባቂዎችን የአሰራር እና የገበያ ስጋቶችን ጨምሮ ለተቋማዊ ስጋቶች ያላቸውን የተጋላጭነት ደረጃ፤

ሐ) የነባር ጠባቂዎችን የገንዘብ ፍሰት ምጣኔዎችን፣ የኡዲት ግኝቶችን፣ የቁጥጥር ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች የሕግ እና የቁጥጥር መስፈርቶችን የማክበር የስራ አፈጻጸም ታሪክ፤ ወይም

መ) የገበያውን ተዓማኒነት እና መዋቅራዊ ስጋትን መቀነስ።

፫/ ባለሥልጣኑ አነስተኛውን የተከፈለ ካፒታል መስፈርት ለመጨመር ሲወስን ለነባር ጠባቂዎች ከስድስት (፮) ወራት ያልበለጠ የሽግግር ጊዜ መስጠት አለበት።

## ክፍል ስድስት

## የውጭ ምንዛሪ፣ የገንዘብ ምንጭ እና ወደ ውጭ ሀገር ማስተላለፍ

**፳፰. ካፒታልን፣ የትርፍ ድርሻን እና ገቢን ወደ ውጭ ሀገር ስለማስተላለፍ**

፩/ የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እና ተፈጻሚነት ያላቸው የብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሪ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር የሚከተሉትን ወደ ውጭ ሀገር ሊዛወሩ የሚችሉ ገቢዎች ሥልጣን በተሰጣቸው መንዛሪዎች በኩል በብቁ የውጭ ሀገር ገንዘብ የማዛወር መብት ይኖረዋል፡-

ሀ) የብድር ሰነደ ሙሳለ ንዋዮች እና የገንዘብ ገበያ ሰነዶች የመክፈያ ጊዜ ሲደርስ የሚገኙ ገቢዎች፤

ለ) ከሰነደ ሙሳለ ንዋዮች ሽያጭ ወይም ዝውውር የሚገኙ ገቢዎች፤

ሐ) የጋራ የኢንቨስትመንት ፈንዶች ክፍልፋዮችን ሽጦ በመውጣት የሚገኙ ገቢዎች፤

መ) የትርፍ ድርሻ፣ ወለድ፣ ኩፖን ወይም ሌሎች ከኢንቨስትመንት የሚገኙ ገቢዎች፤

ሠ) ከሰነደ ሙሳለ ንዋይ ግብይቶች የተገኘ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም፤ እና

ረ) ከተፈቀዱ ኢንቨስትመንቶች በሕጋዊ መንገድ የተገኘ ሌላ ማንኛውም ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዘ ገቢ።

፪/ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ወደ ውጭ ሀገር ማዛወር ተፈጻሚ የሚሆነው የሚከተሉት ከተሟሉ በኋላ ብቻ ነው፡-

ሀ) ኢንቨስተሩ በዚህ ደንብ የተደነገገውን ለኢንቨስትመንቱ ተፈጻሚ የሚሆነውን የይዞታ ጊዜ ሙሉ በሙሉ ሲያሟላ፤

ለ) የሚመለከታቸው የሰነደ ሙሳለ ንዋይ ግብይቶች ክፍያ ሲፈጸም፤

ሐ) ተፈጻሚ የሆኑ ሁሉም ታክሶች፣ ክፍያዎች እና ሌሎች ተዛማጅ ክፍያዎች ሲከፈሉ፤ እና

መ) በባለሥልጣኑ እና በብሔራዊ ባንኩ የተደነገጉ የሪፖርት አቀራረብ እና የሰነድ መስፈርቶች ሲሟሉ።

፫/ የተመዘገበ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር የነዋሪነት ሁኔታ ከኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ወደ የኢትዮጵያ ነዋሪነት የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ ለብሔራዊ ባንክ እና ለባለሥልጣኑ የቅድሚያ ማሳወቂያ የሚጠይቅ ሲሆን፣ ከዚያም የብሔራዊ ባንኩ አግባብነት ያላቸው ሕጎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

፬/ ወደ ውጭ ሀገር የማስተላለፍ ጥያቄዎች የሚያስፈልጉት ሰነዶች በሙሉ ከቀረቡ በኋላ በብሔራዊ ባንክ ተፈጻሚ የውጭ ምንዛሪ ሕጎች በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መስተናገድ አለባቸው።

**፳፱. ጊዜያዊ የካፒታል ፍሰት አስተዳደር እርምጃዎች**

፩/ የዚህ ደንብ ማንኛውም ድንጋጌ ቢኖርም፣ ብሔራዊ ባንክ በልዩ ሁኔታዎች የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ካፒታልን፣ ገቢዎችን፣ የትርፍ ድርሻን፣ ወለድን ወይም ሌሎች ገቢዎችን ወደ ውጭ ሀገር ማዛወርን ለመገደብ፣ ለማዘግየት ወይም በቅድመ ሁኔታ ለማስገዛት ጊዜያዊ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሱት ልዩ ሁኔታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፤ ሆኖም በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም፡-

ሀ) ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ መጠባበቂያ እጥረት፤

ለ) በፋይናንስ ስርዓቱ ላይ የሚከሰት መዋቅራዊ ጫና፤

ሐ) የውጭ ክፍያ ሚዛን ቀውስ ወይም የቀውሱ ጉልህ ስጋት፤ ወይም

መ) በብሔራዊ ባንክ አስተያየት የፋይናንስ ስርዓቱን ያሰጋሉ ተብለው የሚታሰቡ ሌሎች ማናቸውም ድንገተኛ ክስተቶች፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወሰድ ማንኛውም እርምጃ፡-

ሀ) ግልጽ እና በወቅቱ ለሕዝብ ይፋ መደረግ፤

ለ) ከሚመለከታቸው ስጋቶች ጋር የተመጣጠነ፤

ሐ) የተወሰነ ጊዜ ያለው እና በየጊዜው ግምገማ የሚደረግበት፤ እና

መ) ተፈጻሚነት ካላቸው ሕጎች እና ከአገሪቱ ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር የተጣጣመ መሆን አለበት፡ ፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤ ሆኖም በእነዚህ ብቻ አይወሰኑም፡-

ሀ) ወደ ውጭ ሀገር የማዛወር ጥያቄዎችን በጊዜያዊነት ማዘግየት ወይም በተራ ማስኬድ፤

ለ) በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ወደ ውጭ ሀገር በሚዛወረው መጠን ላይ የቁጥር ገደቦችን መጣል፤ ወይም

ሐ) ተጨማሪ የአሰራር ወይም የሰነድ መስፈርቶችን ማስቀመጥ፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚወሰድ ማንኛውም የካፒታል ፍሰት አስተዳደር እርምጃ ተፈጻሚነት ባለው ሕግ መሠረት ካልታደሰ በስተቀር ከመቶ ሰማንያ (፩የ፹) ቀናት በላይ ጸንቶ መቆየት የለበትም፡፡

**፴. ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንቶች የሚያስፈልግ አነስተኛ የይዞታ ጊዜ**

፩/ በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች በሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው አነስተኛ የይዞታ ጊዜ ከአንድ (፩) ዓመት ማነስ የለበትም፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው የይዞታ ጊዜ የሚከተሉትን ከግምት በማስገባት በባለሥልጣኑ በመመሪያ ሊወሰን፣ ሊሰረዝ፣ ሊስተካከል፣ ሊነሳ ወይም ልዩነት ሊደረግበት ይችላል፡-

ሀ) ባለሥልጣኑ በሚያወጣቸው ተጨባጭ የመጠን አመላካቾች የሚለካውን የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያውን ሁኔታ፣ የገንዘብ ፍሰት እና የዕድገት ደረጃ፤

ለ) የአክሲዮን ሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን እና የብድር ሰነዶችን ጨምሮ የገንዘብ ሰነዱን ዓይነት፤

ሐ) የሰነዱ የመክፈያ ጊዜ ወይም ቀሪ የቆይታ ጊዜ፤

መ) ኢንቨስትመንቱ የተተመነበት ገንዘብ፤ እና

ሠ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ መደብ፣ የኢንቨስትመንት ቆይታ ወይም የስጋት ገጽታ፤

ረ) በአዋጁ ከተቀመጡት የባለሥልጣኑ ዓላማዎች ጋር የሚጣጣም ሌላ ማንኛውም ተጨባጭ መመዘኛ፡፡

፫/ ማንኛውም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በባለሥልጣኑ በግልጽ ካልተፈቀደ በስተቀር ተፈጻሚ የሆነው የይዞታ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ከኢንቨስትመንቱ ጋር በተያያዘ ካፒታልን፣ ገቢዎችን ወይም ገቢን ወደ ውጭ ሀገር ማዛወር አይችልም።

፬/ ባለሥልጣኑ የይዞታ ጊዜ መስፈርቶችን በየጊዜው የሚገመግም ሲሆን፣ መስፈርቶቹ እንዲጣሉ ምክንያት የሆኑት ሁኔታዎች ሲያከትሙ መስፈርቶቹን ለማንሳት በማቀድ አስፈላጊ የሆኑ ማስተካከያዎችን በሂደት ያደርጋል።

፭/ በገንዘብ ገበያ ሰነዶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው የይዞታ ጊዜ በብሔራዊ ባንክ ይወሰናል።

## ክፍል ሰባት

## ቀጣይ ግዴታዎች፣ መረጃ ይፋ ማድረግ እና ሪፖርት አቀራረብ

**ክፍፍል. መርህ**

፩/ ሁሉም የተመዘገቡ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች የዚህን ደንብ የምዝገባ መስፈርቶች በማንኛውም ጊዜ ማከበር አለባቸው።

፪/ የተሰየመው ጠባቂ ከተመዘገቡ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮቹ እና ከኢንቨስትመንት ተግባሮቻቸው ጋር የተያያዙ የሚጠየቁ መረጃ ይፋ ማድረጊያዎችን እና ሪፖርቶችን በዚህ የደንቡ ክፍል በተደነገገው አኳኋን፣ ቅጽ እና ድግግሞሽ መሠረት ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

፫/ በዚህ የደንቡ ክፍል መሠረት የሚቀርቡ መረጃ ይፋ ማድረጊያዎች እና ሪፖርቶች የተሟሉ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መሆን አለባቸው፤ እንዲሁም አሳሳች መሆን ወይም ወሳኝ መረጃን መተው የለባቸውም።

፬/ በዚህ ክፍል መሠረት የሚኖሩ ቀጣይ ግዴታዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

ሀ) ጠቅላላ የሕግ ተገዥነት ግዴታዎች፤

ለ) ወቅታዊ የመረጃ ይፋ ማድረግ ግዴታዎች፤ እና

ሐ) ወቅታዊ ጊዜ ጠብቆ የሚደረግ መረጃ ይፋ ማድረግ እና የሪፖርት አቀራረብ ግዴታዎች።

**ክፍፍ. አጠቃላይ ቀጣይነት ያላቸው የህግ ተገዥነት ግዴታዎች**

፩/ የተሰየመ ጠባቂ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ በማንኛውም ጊዜ የሚከተሉትን መፈጸሙን ማረጋገጥ አለበት፡-

ሀ) በዚህ ደንብ መሠረት ያለውን የብቁነት እና የምዝገባ ሁኔታን ጠብቆ መቆየት፤

ለ) በዚህ ደንብ የተቀመጡትን የብቁና ተገቢነት መስፈርቶች ማሟላት፤

ሐ) ተፈጻሚነት ያላቸውን በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል ሕጎችን እና ማዕቀቦችን ማክበር፤

መ) ተፈጻሚነት ያላቸውን የኢንቨስትመንት ገደቦችን፣ የዘርፍ ክልከላዎችን እና የባለቤትነት ጣሪያዎችን ማክበር፤

ሠ) ማንኛውንም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ፈቃድ ባላቸው አገናኞች እና በጸደቁ የገበያ መሰረተ-ልማቶች በኩል ማከናወን፤ እና

ረ) በባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊደነገጉ የሚችሉ ተጨማሪ መስፈርቶችን ማሟላት።

፪/ የተሰየመ ጠባቂ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ በካፒታል ገበያ አዋጁ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች የተከለከሉ የግብይት ተግባራትን እንዳይፈጽም ሁሉንም ምክንያታዊ እርምጃዎች መውሰድ አለበት፡
፡

**፴፫. ወቅታዊ መረጃን ይፋ ስለማድረግ**

፩/ የተመዘገበ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፪ የተዘረዘሩትን መረጃዎች ጨምሮ ማንኛውንም ወሳኝ መረጃ ወዲያውኑ ለተሰየመው ጠባቂው ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ የተሰየመ ጠባቂ የሚከተሉትን መረጃዎች ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ፸፪ ሰዓታት ውስጥ ለባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡-

ሀ) የኢንቨስተሩን ብቁነት፣ የቁጥጥር ሁኔታ፣ ባለቤትነት ወይም እንደ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ኢንቨስት የማድረግ አቅሙን በጉልህ ሁኔታ የሚነካ፤ ወይም

ለ) በገበያ ተዓማኒነት፣ የኢንቨስተሮች ጥበቃ ወይም የፋይናንስ መረጋጋት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል መረጃ፡፡

**፴፬. መረጃ ይፋ ማድረግን የሚያስገድዱ ክስተቶች**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፫ የተመለከቱት አጠቃላይ የመረጃ ይፋ ማድረግ ግዴታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የተሰየመው ጠባቂ እንደአግባብነቱ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩን ወይም የተሰየመውን ጠባቂ የሚመለከቱ ከሚከተሉት ክስተቶች አንዱ ሲከሰት ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ይፋ ማድረግ አለበት፡-

ሀ) በሕጋዊ አቋም፣ በስም፣ በመኖሪያ፣ በነዋሪነት ወይም በቁጥጥር ፈቃድ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ፤

ለ) እዳን መክፍል ያለመቻል፣ የሃብት የማጣራት ሂደት ውስጥ መግባት፣ በሞግዚት አስተዳዳር ስር የመሆን ወይም ተመሳሳይ የሆኑ ክሶች መጀመር ወይም የኪሳራ መታወጅ፤

ሐ) በማንኛውም የሀገር ውስጥ ወይም የውጭ ሀገር ተቆጣጣሪ አካል የሚደረግ ምርመራ፣ የማስፈጸም ወይም የቁጥጥር እርምጃዎች፤

መ) በማናቸውም አገራዊ ወይም ዓለም አቀፍ አካላት የሚጣል ማዕቀብ ወይም መሰል የሚደረግ ስያሜ፤

ሠ) በባለቤትነት፣ በቁጥጥር፣ በድምጽ አሰጣጥ አደረጃጀቶች ወይም በኢንቨስትመንት ስልት ላይ የሚደረግ ጉልህ ለውጥ፤

ረ) በተጠቃሚ ባለቤትነት ላይ የሚደረግ ማንኛውም ለውጥ፤ ወይም

ሰ) በባለሥልጣኑ ወሳኝ ነው ተብሎ የሚወሰን ሌላ ማንኛውም ክስተት፡፡

**፴፭. የተጠቃሚ ባለቤትነትን ይፋ ስለማድረግ**

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በተመዘገበ አውጪ የሚይዘው ድርሻ ከአውጪው የተከፈለ ካፒታል አምስት በመቶ (፭%) ሲደርስ ወይም ሲበልጥ ጥቅም ያለው ሰው ስለመሆኑ በተሰየመው ጠባቂው በኩል ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ ይፋ የሚደረጉ መረጃዎች ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

ሀ) የአውጪው ስም፤

ለ) የተያዙት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች መደብ እና ባህሪ፤

ሐ) ከአውጪው አጠቃላይ የተከፈለ ካፒታል አንጻር የይዞታው መጠን እና መቶኛ፤

መ) የሚመለከተው የባለቤትነት ለውጥ የተከሰተበት ቀን፤

ሠ) የተጠቃሚ ባለቤቱን ማንነት፤

ረ) የሚደረገው ቁጥጥር ወይም ተጽዕኖ ባህሪ እና መጠን፤ እና

ሰ) በባለሥልጣኑ የሚወሰን ሌላ ማንኛውም ተጨማሪ መረጃ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰውን መቶኛ ሲሰላ ይዞታዎች በአውጪው ቅርበት ባላቸው ተቋማት፣ በጋራ በሚንቀሳቀሱ ሰዎች እንዲሁም በሁሉም ቀጥተኛ፣ ተዘዋዋሪ ወይም የተጠቃሚ ባለቤትነት ዓይነቶች ተጠቃለው ይታሰባሉ።

፬/ የተጠቃሚ ባለቤትነት መረጃን ይፋ አለማድረግ በባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ያስከትላል።

**፴፮. የተሰየመ ጠባቂ ወቅታዊ ጊዜ ጠብቆ የሪፖርት የማቅረብ ግዴታዎች**

፩/ ወቅታዊ ጊዜ ጠብቀው የሚቀርቡ ሪፖርቶች ከሪፖርት ማቅረቢያው ጊዜ ጋር የተያያዙ ትክክለኛ እና የተሟሉ መረጃዎችን የሚይዙ ሆነው ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-

ሀ) የኢንቨስትመንቶችን አጠቃላይ ዋጋ ጨምሮ በእያንዳንዱ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር፣ በሰነድ ዓይነት፣ በብዛት እና በገበያ ዋጋ የተዘረዘረ የፖርትፎሊዮ ይዞታ መግለጫ፤

ለ) በወቅቱ የተፈጸሙ የግዥዎች፣ የሽያጮች፣ የግዢ ቃል ኪዳኖችን፣ የመልሶ ግዥዎች እና የሌሎች ግብይቶች ዝርዝር፤

ሐ) በሀብት መደብ፣ በዘርፍ እና በአውጪ የተከፋፈለ የተጠቃለለ ተጋላጭነት፤

መ) በባለቤትነት፣ በቁጥጥር፣ በድምጽ አሰጣጥ አደረጃጀቶች ወይም በኢንቨስትመንት ስልት ላይ የተደረጉ ማናቸውም ለውጦች ዝርዝር፤

ሠ) የኢንቨስትመንት ገደቦች እና የባለቤትነት ጣሪያዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጥ ማረጋገጫ፤

ረ) ባለሥልጣኑ የዚህን ደንብ እና አግባብነት ያላቸውን መመሪያዎች መከበር ለመገምገም የሚያስፈልገው ሌላ ማንኛውም መረጃ።

፪/ የተሰየመ ጠባቂ የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፡-

ሀ) የመደብ ፪ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን በተመለከተ እያንዳንዱ ወር ካበቃ በኋላ ባሉት ሰባት (፯) የካላንደር ቀናት ውስጥ ወርሃዊ ሪፖርት፤

ለ) የመደብ ፩ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን በተመለከተ እያንዳንዱ ሩብ ዓመት ካበቃ በኋላ ባሉት ሠላሳ (፴) የካላንደር ቀናት ውስጥ የሩብ ዓመት ሪፖርት፤ እና

ሐ) እያንዳንዱ የሂሳብ ዓመት ካበቃ በኋላ ባሉት ዘጠና (፺) የካላንደር ቀናት ውስጥ ዓመታዊ ሪፖርት።

፫/ ባለሥልጣኑ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የተለያዩ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር መደቦች ላይ የተለያዩ የሪፖርት አቀራረብ መስፈርቶችን ተፈጻሚ ሊያደርግ ወይም የተጠናከረ መረጃ ይፋ ማድረግ ወይም ማረጋገጫ ሊጠይቅ ይችላል፡-

ሀ) የኢንቨስትመንቶቹ መጠን፣ ውስብስብነት እና ክምችት፤

ለ) የኢንቨስተሩ የስጋት ደረጃ እና የግብይት ባህሪ፤ እና

ሐ) በገበያ ተዓማኒነት፣ በኢንቨስተሮች ጥበቃ ወይም በፋይናንስ መረጋጋት ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ፤

መ) ባለሥልጣኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ሌሎች ጉዳዮች።

**፴፯. በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በርካታ የግብይት ሂሳቦችን ስለመጠቀም**

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ ዓላማ ፈቃድ ካላቸው ከአንድ ወይም ከዚያ በላይ ደላሎች ጋር በርካታ የግብይት ሂሳቦችን ሊከፍት እና ሊያንቀሳቅስ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም፣ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ለሁሉም የቁጥጥር ዓላማዎች እንደ አንድ ሕጋዊ እና ተጠቃሚ ኢንቨስተር ይቆጠራል።

፫/ በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር የሚከፈቱ ሁሉም የግብይት ሂሳቦች ከአንድ የተሰየመ ጠባቂ ጋር የተገናኙ መሆን አለባቸው፤ የተሰየመው ጠባቂም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ ኢንቨስትመንቶች በማዕከላዊ

የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት መዝገብ ውስጥ ከአንድ ሂሳብ ብቻ ጋር መተሳሰራቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፬/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ በሁሉም የግብይት ሂሳቦች የሚገኙ ይዞታዎች እና ግብይቶች ለሚከተሉት ዓላማዎች ተጠቃለው ይታሰባሉ፡-

ሀ) የባለቤትነት ገደቦችን እና የገበያ ስነ-ምግባርን ለመከታተል፤

ለ) ለሪፖርት አቀራረብ እና ለመረጃ ይፋ ማድረግ፤ እና

ሐ) ምንዛሪን ወደ ውጭ ሀገር ለማዛወር፡፡

**፴፫. የመዝገብ አያያዝ ግዴታዎች**

፩/ የተሰየመው ጠባቂ በዚህ ደንብ መሠረት በተመዘገቡ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮቹ የተከናወኑ ሁሉንም የኢንቨስትመንት ተግባራት የተሟላ፣ ትክክለኛ እና ወቅታዊ መዝገብ መያዝ አለበት፡፡

፪/ መዝገቦች ታማኝነታቸውን በሚጠብቅ፣ መለወጥን ወይም መጥፋትን በሚከላከል እንዲሁም በወቅቱ ተደራሽ እንዲሆኑ እና ሊነበብ በሚችል መልኩ እንዲባዙ በሚያስችል አኳኋን ቢያንስ ለአስር (፲) ዓመታት መቀመጥ አለባቸው፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ በማንኛውም ጊዜ የተሰየመው ጠባቂ ለምርመራ፣ ለኦዲት ወይም ለቁጥጥር ዓላማ መዝገቦችን ወይም ቅጂዎቻቸውን እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፴፬. የአውጪዎች የሪፖርት ግዴታዎች**

፩/ በባለሥልጣኑ አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች መሠረት ካሉት ቀጣይ የመረጃ ይፋ ማድረግ ግዴታዎች አካል እንደመሆኑ፣ አውጪው መረጃው በአውጪው ዘንድ የሚታወቅ ወይም በባለአክሲዮኖች መዝገቡ በምክንያታዊነት ሊረጋገጥ የሚችል እስከሆነ ድረስ በዚህ ደንብ የተደነገጉትን የመረጃ ይፋ ማድረጊያ ጣሪያዎች የሚደርስ ወይም የሚበልጥ ማንኛውንም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ይዞታ፣ የባለቤትነት ለውጥ ወይም የድምጽ መስጫ ጥቅም የመከታተል እና ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፪/ አውጪው ተፈጻሚነት ያላቸውን የውጭ ባለቤትነት ገደቦችን፣ የባለቤትነት ጣሪያዎችን ወይም ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ጋር የተያያዘ ሌላ ማንኛውንም የቁጥጥር መስፈርት መከበርን የሚነካ ማንኛውንም ከውጭ ባለቤትነት ጋር የተያያዘ ክስተት ወይም ለውጥ ባለሥልጣኑ በሚደነግገው ቅጽ እና አኳኋን ወዲያውኑ ለባለሥልጣኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በአውጪው የሚደረጉ መረጃን ይፋ የማድረግ ተግባራት ትክክለኛ፣ የተሟሉ እና ወቅታዊ መሆን ያለባቸው ሲሆን አሳሳች መሆን ወይም ጉልህ መረጃን መተው የለባቸውም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት መረጃን ይፋ አለማድረግ በባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃን ያስከትላል፡፡

## ክፍል ስምንት

## መዋቅራዊ ስጋት፣ የጥንቃቄ መከላከያዎች እና የገበያ መረጋጋት

**፴፭. መዋቅራዊ ስጋት ክትትል እና የገበያ መረጋጋት መከላከያዎች**

፩/ ባለሥልጣኑ ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ተግባራት የሚመነጨውን መዋቅራዊ የአደጋ ስጋት በቀጣይነት ለመከታተል እና ለመገምገም የሚያስችሉ ስርዓቶችን እና አሰራሮችን መዘርጋት አለበት፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ዓላማ ባለሥልጣኑ ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ የሚከተሉትን ሊገመግም ይችላል፡-

ሀ) በአውጪዎች እና በዘርፎች መካከል ያለውን የውጭ ፖርትፎሊዮ ባለቤትነት የስጋት ክምችት፤

ለ) የተጠቃለሉ የውጭ ፖርትፎሊዮ ገቢ ፍሰቶችን እና መቀልበሶችን መጠን፣ ስብጥር እና መዋዠቅ፤

ሐ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን የሀብት መደብ ተጋላጭነት እና ብዝሃነት መከታተል፤

መ) በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያው ውስጥ ያለውን የዋጋ መዋዠቅ እና የገንዘብ አከልነት ሁኔታ፤

ሠ) በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ተግባራት ላይ በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ በካፒታል ገበያ መሰረተ-ልማቶች እና በፋይናንስ ተቋማት መካከል ያለውን የስጋት መዛመት ተጽዕኖ፤

ረ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ስጋት ወደ ፋይናንስ ስርዓቱ ሊዛመት የሚችልበትን ሁኔታ፤

ሰ) የድንበር ተሻጋሪ የቁጥጥር ትብብር፣ የመረጃ ልውውጥ እና የተቀናጁ እርምጃዎች በቂነት፤ እና

ሸ) መዋቅራዊ ስጋትን ለመገምገም ባለሥልጣኑ አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸው ሌሎች ጉዳዮች።

፫/ ባለሥልጣኑ ሚስጥራዊ ወይም ሚስጥራዊነት ያላቸው መረጃዎች ማንነታቸው እንዳይታወቅ በማድረግ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንትን ተጽዕኖ የሚገመግም የመዋቅራዊ ስጋት እና የገበያ መረጋጋት ሪፖርት ተገቢ ነው ብሎ በሚያስበው የጊዜ ልዩነት ማዘጋጀት እና ይፋ ማድረግ አለበት።

፬/ ወሳኝ ወይም አዳዲስ የሚከሰቱ መዋቅራዊ ስጋቶች ሲለዩ ባለሥልጣኑ፦

ሀ) ቅድመ ማስጠንቀቂያዎችን፣ መመሪያዎችን ወይም አስተያየቶችን ሊሰጥ፤

ለ) ለካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና ለገበያ መሰረተ-ልማቶች የጥንቃቄ መስፈርቶችን ሊያስፈጽም፤

ሐ) ከሚመለከታቸው የገበያ ተሳታፊዎች የተጠናከረ ሪፖርት አቀራረብ ወይም መረጃ ይፋ ማድረግ ሊጠይቅ፤

መ) የተለዩትን ስጋቶች ለመቀነስ በዚህ ደንብ መሠረት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተመጣጣኝ እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል።

፭/ ባለሥልጣኑ ይህንን አንቀጽ ተግባራዊ ለማድረግ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**<u>፵፩</u>. የቅድመ ማስጠንቀቂያ ጠቋሚዎች እና የቁጥጥር ምላሽ**

<u>፩</u>/ ባለሥልጣኑ ከብሔራዊ ባንክ ጋር በመቀናጀት ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ አዳዲስ የሚከሰቱ ስጋቶችን ለመለየት የሚያስችሉ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ጠቋሚዎችን ሊያዘጋጅ ይችላል።

<u>፪</u>/ ባለሥልጣኑ ከብሔራዊ ባንክ ጋር በመተባበር በሚከተሉት ሳይወሰን የቅድመ ማስጠንቀቂያ ጠቋሚዎችን በሥርዓት ማካተት እና መለየት አለበት፤

ሀ) ፈጣን የሀብት ዋጋ ንረት፤

ለ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ገቢ እና ወጪ ፍሰቶች ከፍተኛ ጭማሪ፤ መቀልበስ ወይም መከማቸት፤

ሐ) የገበያ መዋዠቅ ወይም የገንዘብ አከልነት ጫና ድንገተኛ ጭማሪ፤

መ) የገበያ ጥልቀት፣ የግዥና ሽያጭ ዋጋ ልዩነት ወይም የዋጋ ግኝት ስርዓቶች መዳከም፤

ሠ) የገበያውን አሰራር የሚነኩ የአሰራር፣ የክፍያ ማጣራት፣ የክፍያ መፈጸም ወይም የጥበቃ መስተጓጎሎች።

<u>፫</u>/ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶቹ የሚከተሉትን ለማከናወን የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማካተት አለባቸው፦

ሀ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ፍሰቶችን፣ የባለቤትነት ደረጃዎችን፣ ክምችትን እና ተዛማጅ የግብይት አካሄድን መከታተል፤

ለ) ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች አገልግሎት የሚሰጡ አገልግሎት ሰጭዎችን የፋይናንስ፣ የአሰራር፣ የጥበቃ እና የክፍያ አፈጻጸም ተጋላጭነቶችን መገምገም፤

ሐ) የካፒታል እና የገንዘብ አከልነት ጫናዎችን፣ የክፍያ መዘግየቶችን፣ የመያዣ እጥረቶችን ወይም የቁጥጥር ገደቦችን ደጋግሞ ለመጣስ መቃረብን ጨምሮ የጫና ጠቋሚዎችን መለየት፤ እና

መ) አገልግሎት ሰጭዎች ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ወይም ለገበያው ያለባቸውን ግዴታዎች የመወጣት አቅም ሊያዳክሙ የሚችሉ ሁኔታዎችን መለየት::

**<u>፵፪</u>. የጥንቃቄ ተጋላጭነት እና የክምችት ቁጥጥሮች**

፩/ ባለሥልጣኑ ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች አገልግሎት የሚሰጡ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና የካፒታል ገበያ መሰረተ-ልማቶች ከእነዚህ ተግባራት ከሚመነጩ ስጋቶች ጋር የተመጣጠኑ የጥንቃቄ መስፈርቶችን እንዲያሟሉ ሊጠይቅ ይችላል:: እነዚህ ግዴታዎች በሚከተሉት ሳይወሰኑ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

ሀ) አገልግሎት ከሚሰጥባቸው የውጭ ፖርትፎሊዮ ግብይቶች መጠን እና ባህሪ ጋር የተመጣጠነ በቂ ካፒታል፣ የገንዘብ አከልነት እና የገንዘብ መጠባበቂያ መያዝ፤

ለ) የክፍያ አፈጻጸም፣ የጥበቃ፣ የተጓዳኝ ወገን፣ የአሰራር እና የክምችት ስጋቶችን የሚመለከቱ ጠንካራ የስጋት አስተዳደር ስርዓቶችን እና የውስጥ ቁጥጥሮችን መተግበር፤

ሐ) ተጨማሪ የአሰራር ጥንካሬ፣ የስራ ቀጣይነት እና ከአደጋ የማገገም መስፈርቶች እና መመዘኛዎችን መጠየቅ፤

መ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን የሚነኩ መስተጓጎሎችን የሚመለከቱ የአሰራር ጥንካሬ እና የስራ ቀጣይነት ዝግጅቶችን መያዝ፤

ሠ) ከሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የገበያ መሰረተ-ልማቶች፣ የፋይናንስ ተቋማት ወይም የክፍያ ስርዓቶች ጋር ያሉ ተጋላጭነቶችን፣ ጥገኝነቶችን ወይም ወሳኝ የአገልግሎት ትስስሮችን ጨምሮ ከመተሳሰር እና ከመተላለፍ ስጋት ጋር የተያያዙ ጣሪያዎችን፣ ገደቦችን ወይም ተጨማሪ መከላከያዎችን ማስቀመጥ::

፪/ ባለሥልጣኑ አንድ አገልግሎት ሰጪ ፡-

ሀ) ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ አገልግሎት ሲሰጥ፤

ለ) ለውጭ ፖርትፎሊዮ የገበያ ተደራሽነት መዋቅራዊ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ ሲገኝ፤ ወይም

ሐ) በቁጥጥር ወይም በቅድመ ማስጠንቀቂያ ስርዓቶች የተለዩ ከፍ ያሉ የስጋት ጠቋሚዎችን ሲያሳይ፡ ፡

የተጠናከሩ ወይም የተለዩ የጥንቃቄ መስፈርቶችን ሊጥል ይችላል።

**<u>፵፫</u>. የገበያ ጫና እና የልዩ ሁኔታዎች እርምጃዎች**

፩/ ባለሥልጣኑ በመዋቅራዊ ስጋት ግምገማዎች ወይም በቅድመ ማስጠንቀቂያ ጠቋሚዎች ላይ በመመስረት ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ የገበያ ጫና ወይም ልዩ ሁኔታዎች መኖራቸውን ወይም ሊከሰቱ እንደሚችሉ ሲወስን ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ጋር በመቀናጀት ተመጣጣኝ እና ጊዜያዊ የገበያ መረጋጋት እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል::

፪/ ለዚህ አንቀጽ ዓላማ የገበያ ጫና ወይም ልዩ ሁኔታዎች በሚከተሉት ሳይወሰኑ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

ሀ) የከፋ ወይም ከመደበኛ ሥርዓት ውጭ የዋጋ መዋዠቅ ወይም ተከታታይ የገንዘብ አከልነት እጥረት፤

ለ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ፍሰቶች ድንገተኛ ጭማሪ፤ መቀልበስ ወይም መከማቸት፤

ሐ) በግብይት፣ በክፍያ ማጣራት፣ በክፍያ አፈጻጸም፣ በጥበቃ ወይም በክፍያ ስርዓቶች ተግባር ላይ የሚደርሱ ጉልህ ስጋቶች፤

መ) የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን፣ የገበያ መሰረተ-ልማቶችን ወይም የፋይናንስ ተቋማትን የሚያካትቱ ከፍ ያሉ የስጋት መዛመት ወይም የመተሳሰር ስጋቶች፤ ወይም

ሠ) በኢንቨስተሮች ጥበቃ ወይም በፋይናንስ መረጋጋት ላይ ጉልህ ስጋት የሚፈጥሩ ሌሎች ሁኔታዎች።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ለተጠቀሱት ሁኔታዎች የሚወሰዱ እርምጃዎች በሚከተሉት ሳይወሰኑ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦

ሀ) የተጠናከረ ወይም በልዩ ሁኔታ የሚቀርብ ሪፖርት፣ መረጃ ይፋ ማድረግ ወይም የማሳወቅ መስፈርቶች፤

ለ) በካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ላይ የካፒታል መጠባበቂያዎችን፣ የገንዘብ አከልነት ጣሪያዎችን ወይም የተጋላጭነት ገደቦችን ጨምሮ በጥንቃቄ መስፈርቶች ላይ የሚደረጉ ጊዜያዊ ማስተካከያዎች፤

ሐ) ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዙ የተወሰኑ የግብይት ተግባራት፣ ሰነዶች ወይም ግብይቶች ላይ የሚጣሉ ጊዜያዊ ገደቦች ወይም የግብይት ማቋረጫዎች፤

መ) የአሰራር ጥንካሬን፣ የክፍያ አፈጻጸም ዲሲፕሊንን ወይም የስጋት አስተዳደር አሰራሮችን ለማጠናከር የሚሰጡ መመሪያዎች፤ ወይም

ሠ) የተለዩትን ስጋቶች ለመፍታት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተመጣጣኝ የቁጥጥር ወይም የክትትል እርምጃዎች።

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚጣሉ እርምጃዎች በስጋት ላይ የተመሰረቱ፣ ተመጣጣኝ እና የጊዜ ገደብ ያላቸው መሆን ያለባቸው ሲሆን በየጊዜው ግምገማ የሚደረግባቸው እና የገበያ ሁኔታዎች ሲረጋጉ የሚነሱ ይሆናሉ።

፭/ ልዩ ሁኔታዎቹ በመመሪያ ከተወሰነው ጊዜ በላይ ሲቀጥሉ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ያለው ሰው የሚከስርበትን ሁኔታ ለመቋቋም የሚያስችሉ የአስቸኳይ ጊዜ እና የማገገሚያ ዕቅዶችን ማዘጋጀት እና እንዲተገበሩ ማድረግ አለበት።

፮/ ለእንደዚህ ዓይነት ኪሳራ የሚዘጋጀው የአስቸኳይ ጊዜ ዕቅድ የሌሎች የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎችን ወይም የገበያ መሰረተ-ልማቶችን ስርዓታዊ ተግባር የማያውክ እና የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮችን ጥቅሞች እና ሀብቶች በበቂ ሁኔታ የሚጠብቅ መሆን አለበት።

## ክፍል ዘጠኝ
## አስተዳደር እና ስነ-ምግባር

**፶፬. የሕግ ተገዥነት እና የውስጥ ቁጥጥር**

፩/ በባለሥልጣኑ የተደነገጉት የስነ-ምግባር እና የአስተዳደር መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች አገልግሎት የሚሰጡ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና የገበያ መሰረተ-ልማቶች ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ የአሰራር ስጋቶችን እና የሕግ ተገዥነትን ለመከታተል የተቀረጸ አጠቃላይ የሕግ ተገዥነት እና ውስጣዊ ቁጥጥር ማዕቀፍ መያዝ አለባቸው።

፪/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር የተሰየመ ጠባቂ ሁሉም የኢንቨስትመንት ገደቦች፣ የሪፖርት ማቅረቢያ ጊዜያት፣ የግብር ግዴታዎች እና ሌሎች የቁጥጥር መስፈርቶች በወጥነት መሟላታቸውን የሚያረጋግጥ የተመደበ የሕግ ተገዥነት መኮንን መሾም አለበት።

**፶፭. የጥቅም ግጭት እና የተሻለ አፈጻጸም**

፩/ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ከውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ የጥቅም ግጭቶችን እና ስጋቶችን ለመለየት እና ለመቀነስ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

፪/ አግባብነት ያላቸው የካፒታል ገበያ ሕጎች፣ ፈቃድ ያላቸው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያዎች ውስጠ-ደንቦች እንዲሁም ከደንበኛው የተሰጠው ትእዛዝ ውሎች እና ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩ ትእዛዞችን በቅን ልቦና ማስተላለፍ እና ግብይቶችን መፈጸም አለበት፡፡

**፴፮. የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ኃላፊነቶች**

፩/ በባለሥልጣኑ አግባብነት ባላቸው መመሪያዎች የተደነገጉት የአስተዳደር እና የስነ-ምግባር መስፈርቶች እና ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ በተገቢ ሙያዊ ጥንቃቄ፣ በቅልጥፍና እና በታማኝነት መስራት አለበት፡፡

፪/ በአግባብነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉ ሌሎች መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ፈቃድ ያላቸው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች፡-

ሀ) የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንት ግብይቶችን በፍትሃዊ፣ ግልጽ እና ስርዓታዊ በሆነ አኳኋን መፈጸም፤

ለ) ተፈጻሚ የሆኑ የኢንቨስትመንት ገደቦች እና የገበያ ደንቦች ሙሉ በሙሉ መከበራቸውን ማረጋገጥ፤

ሐ) ሁሉንም ክፍያዎች፣ ኮሚሽኖች እና ወጪዎች በግልጽ እና በተገቢው አኳኋን ይፋ ማድረግ፤ እና

መ) ተፈጻሚ የሆኑ ሕጎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ ውጤታማ የአሰራር ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን መዘርጋት፤

አለባቸው።

፫/ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንትን የሚያካትቱ ግብይቶችን በተመለከተ ሪፖርቶችን እና ተዛማጅ መረጃዎችን አግባብነት ባላቸው ደንቦች እና ውስጠ-ደንቦች መሠረት ከወቅታዊ ሪፖርቶቹ ጋር ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት፡፡

**፴፯. የተሰየመ ጠባቂ ተግባራት እና ኃላፊነቶች**

፩/ የተሰየመ ጠባቂ፡-

ሀ) ተገቢ ጥንቃቄ እና ሙያዊ ብቃት ማሳየት፤

ለ) በደንበኞቹ በመወከል የሚደረጉ ግብይቶችን በተመለከተ ምስጢራዊነትን መጠበቅ፤

ሐ) ከባለሥልጣኑ ምርመራዎች ጋር መተባበር፤

መ) በባለሥልጣኑ ትእዛዝ ሲሰጠው ያልተፈቀዱ ግብይቶችን ለመከላከል የሰነደ ሙዓለ ንዋዮችን ሽያጭ ወይም ዝውውር መገደብ፤

ሠ) ከፍተኛ የታማኝነት፣ የስነ-ምግባር እና የብቁና ተገቢነት መስፈርቶችን ማከበር፤ እና

ረ) በባለሥልጣኑ የተወሰኑ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን አለበት፡፡

፪/ የተሰየሙ ጠባቂዎች ከሕግ ወይም ከቁጥጥር ግዴታዎች መጣስ ለሚመነጩ ኪሳራዎች ወይም ጉዳቶች ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

**፴፰. የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ግዴታዎች**

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር፡-

ሀ) ለጠባቂው እና ለባለሥልጣኑ አሳሳች፣ ሐሰተኛ እና ትክክል ያልሆነ መረጃ ማቅረብ የለበትም፤

ለ) የባለቤትነት ገደቦችን፣ የመረጃ ይፋ ማድረግ ጣሪያዎችን ወይም የኩባንያ ቁጥጥር ግዥ ደንቦችን ለማምለጥ ኢንቨስትመንቶችን ማዋቀር የለበትም፤

ሐ) አገልግሎት ሰጪዎችን በመሾም ረገድ ተገቢ ጥንቃቄ ማድረግ እና የጸና ፈቃድ እንዳላቸው ማረጋገጥ አለበት፤

መ) በብሔራዊ ባንክ፣ በባለሥልጣኑ እና በተሰየመው ጠባቂ ለሚቀርብ ማንኛውም ምክንያታዊ የመረጃ ጥያቄ ወዲያውኑ እና በትክክል ምላሽ መስጠት አለበት፤ እና

ሠ) በዚህ ደንብ እና በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች የተደነገጉትን የተጠቃሚ ባለቤትነት እና የመረጃ ይፋ ማድረግ መስፈርቶችን፣ የገቢያ ስነ-ምግባርን እንዲሁም በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል ደንቦችን እና መመዘኛዎችን ማክበር አለበት፡፡

፪/ ተቋማዊ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር የመልካም የኩባንያ አስተዳደር መመዘኛዎች እና ሌሎች ተፈጻሚ የሆኑ ምርጥ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

## ክፍል አስር
## የኢንቨስተሮች ጥበቃ፣ የቅሬታ እና የግጭት አፈታት

**፶፱. ያለአድልዎ እና በፍትሃዊነት ስለመስተናገድ**

፩/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች በተመሳሳይ ሁኔታዎች ውስጥ ላሉ የሀገር ውስጥ ኢንቨስተሮች ከሚሰጠው ያላነሰ አያያዝ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

፪/ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ድምጽ የመስጠት መብቱን የመጠቀም እንዲሁም ከኢንቨስትመንቱ የሚመነጩ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅሞችን፣ የትርፍ ድርሻን፣ ወለድን እና ሌሎች ሕጋዊ ገቢዎችን የመቀበል መብት አለው፡፡

፫/ በዚህ ደንብ ወይም በሌሎች ተፈጻሚነት ባላቸው ሕጎች በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር በውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች ላይ ምንም ዓይነት ገደብ፣ ክልከላ ወይም አስተዳደራዊ እርምጃ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**፷. የካሳ ፈንድ**

የኢንቨስተሮች ካሳ ፈንድ ፈቃድ ያለው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ እና የሰነደ ሙሳለ ንዋዮች ገበያ በመከሰራቸው ምክንያት የገንዘብ ኪሳራ ለደረሰባቸው ብቁ መደበኛ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች በካፒታል ገበያ ካሳ ፈንድ ደንብ እና መመሪያ መሠረት ባሉት የሽፋን ገደቦች እና አሰራሮች መሠረት ካሳ ይከፍላል፡፡

**፷፩. ለባለሥልጣኑ ቅሬታ ስለማቅረብ**

፩/ በስራ ላይ ያሉ ሕጎች እንደተጠበቁ ሆነው የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች እና የገበያ መሰረተ-ልማቶች የውስጥ ቅሬታ ማስተናገጃ ስርዓቶች መያዝ አለባቸው፡፡

፪/ በዚህ ደንብ መሠረት ኃላፊነት ባለባቸው ሰዎች ቅር የተሰኘ ማንኛውም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ለባለሥልጣኑ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ቅሬታዎችን ለማቅረብ፣ ማብራሪያ ለመጠየቅ ወይም ስጋቶችን ለማንሳት የሚያስችሉ ግልጽ፣ ተደራሽ እና የተደራጁ ስርዓቶችን መዘርጋት አለበት፡፡

፬/ ቅሬታ የሚያቀርቡ ኢንቨስተሮች ከማንኛውም ዓይነት የበቀል እርምጃ፣ አድሎአዊ አያያዝ ወይም ጉዳት የሚያስከትል አያያዝ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

፭/ ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀረበለትን ማንኛውንም ቅሬታ መርምሮ ቅሬታው ከደረሰው ቀን ጀምሮ ባሉት ሠላሳ (፴) ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፤ ሆኖም በጉዳዩ ውስብስብነት፣ ተጨማሪ መረጃ በማስፈለጉ ወይም በሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ረዘም ያለ ጊዜ የሚያስፈልግ ሲሆን ውሳኔው ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፺ ቀናት ውስጥ መሰጠት አለበት፡፡

፮/ ከኢንቨስተሩ ተጨማሪ መረጃ የሚያስፈልግ ሆኖ ኢንቨስተሩ መረጃውን ወይም ማስረጃውን ያላቀረበ እንደሆነ የጊዜ ቆጠራው ይታገዳል፡፡

፫/ በባለሥልጣኑ የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሳኔ ቅር የተሰኘ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በአዋጁ መሠረት ለካፒታል ገበያ አስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

**፶፪. የአለመግባባቶችን ስለመፍታት**

በካፒታል ገበያው ውስጥ የሚነሱ የፍትሐብሔር አለመግባባቶች በእርቅ የሚፈቱ ሲሆን፣ እርቁ ካልተሳካ በአዋጁ እና በባለሥልጣኑ መመሪያዎች መሠረት በግልግል ዳኝነት ይፈታሉ፡፡

## ክፍል አስራ አንድ

## ሕግ ማስከበር እና ቅጣቶች

**፶፫. አስተዳደራዊ እርምጃዎች**

፩/ ባለሥልጣኑ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ወይም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የዚህን ደንብ ማንኛውንም ድንጋጌ መጣሱን ሲያረጋግጥ ከጥሰቱ ባህሪ እና ክብደት ጋር በሚመጣጠን መልኩ ከሚከተሉት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አንዱን ወይም በጣምራ ሊወስድ ይችላል፡-

ሀ) ይህንን ደንብ የሚጥስ ማንኛውም ድርጊት ወይም ግድፈት እንዲቆም ማዘዝ፤

ለ) የሚመለከተው ሰው የተወሰኑ ተግባራትን እንዲያቆም ወይም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የማስተካከያ እርምጃዎችን እንዲወስድ ማዘዝ፤

ሐ) ከጥሰቱ ክብደት፣ ቆይታ እና ተጽዕኖ ጋር የሚመጣጠን አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት መጣል፤

መ) በባለሥልጣኑ የተሰጠውን ምዝገባ፣ ፈቃድ ወይም ይሁንታ ማገድ ወይም መሰረዝ፤

ሠ) በካፒታል ገበያው ውስጥ የሚደረግ ግብይት ወይም ተሳትፎ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ማገድ፣ መገደብ ወይም መከልከል፤ ወይም

ረ) በዚህ ደንብ መሠረት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ የተደነገገ ሌላ ማንኛውንም አስተዳደራዊ እርምጃ መጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በዚህ ደንብ ላይ የሚፈጸም ጥሰትን ያመቻቸ፣ ያገዘ፣ ያነሳሳ ወይም ጥሰቱን ለመከላከል ተገቢ ጥንቃቄ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ባለሥልጣኑ በንዑስ አንቀጽ (፩) ከተደነገጉት አስተዳደራዊ እርምጃዎች አንዱን ወይም በማጣመር በአገልግሎት ሰጪው ላይ ሊጥል ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ የጥሰቱን ባህሪ፣ ክብደት፣ ቆይታ እና ተጽዕኖ እንዲሁም የሚመለከተውን ሰው የኃላፊነት መጠን ከግምት በማስገባት ለተወሰኑ የዚህ ደንብ ጥሰቶች ተፈጻሚ የሚሆኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን እና የቅጣት ወሰኖችን በመመሪያ ይወስናል፡፡

፬/ ባለሥልጣኑ ኢንቨስተሩ ወይም አገልግሎት ሰጪው በካፒታል ገበያ አዋጁ የተከለከሉ የግብይት ተግባራትን መፈጸሙን ሲያረጋግጥ አስተዳደራዊ የገንዘብ ቅጣት እና ሌሎች አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ከመጣል በተጨማሪ የተገኘው የገንዘብ ጥቅም ለተጎዱ የገበያ ተሳታፊዎች እንዲመለስ ሊያዝ ይችላል፡፡

**፶፬. ማገድ፣ መገደብ እና መሰረዝ**

፩/ ባለሥልጣኑ በመካሄድ ላይ ያለ ምርመራ ሲኖር የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ፈቃድ ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ ላይ የመገበያየት መብቱን በጊዜያዊነት ሊያግድ ይችላል፡፡

፪/ በከባድ ቸልተኝነት፣ በማጭበርበር ወይም ጥሰቱ ተደጋጋሚ በሆነበት ሁኔታ ባለሥልጣኑ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሩን ምዝገባ በቋሚነት ሊሰርዝ እና በኢትዮጵያ ያለው ፖርትፎሊዮው በሥርዓት እንዲሸጥ ሊያዝ ይችላል፡፡

፫/ ባለሥልጣኑ ጉልህ ጥሰት ፈጽሟል ተብሎ የተረጋገጠበትን ማንኛውንም የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ውስጥ እንዳይሳተፍ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ሊከለክል ይችላል፡፡

**፶፩. የተከለከሉ ድርጊቶች**

፩/ የሚከተሉት ጥሰቶች በባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ያስከትላሉ፡-

ሀ) ብቁ ሰነዶች ተብለው ባልተዘረዘሩ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት ማድረግ፤

ለ) ከተፈቀዱ የገንዘብ ሰነዶች ውጭ ኢንቨስት ማድረግ፤

ሐ) የባለሥልጣኑን ይሁንታ ሳያገኙ ከተወሰነው የባለቤትነት ገደብ በላይ መያዝ፤

መ) ከገደቡ በላይ የሆነውን የአክሲዮን ባለቤትነት ጥሰቱ ከተፈጸመ በኋላ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አለመሸጥ፤

ሠ) ቅርበት ባላቸው ተቋማት በኩል ወይም በመቀናጀት በመንቀሳቀስ ጣሪያዎችን ማለፍ፤

ረ) ያለ የተሰየመ ጠባቂ ኢንቨስት ማድረግ፤

ሰ) ከአንድ የማዕከላዊ የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ግምጃ ቤት ሂሳብ ጋር ያልተሰሩ የግብይት ሂሳቦችን ማንቀሳቀስ፤

ሸ) ደንበኛን የማወቅ እና የተገቢነት ቁመና ጥናት ሳይደረግ ሂሳቦችን መክፈት፤

ቀ) ቀጣይነት ያላቸውን ግዴታዎችን አለማከበር፤

በ) የሚጠየቁ የመረጃ ይፋ ማድረጊያዎችን ወይም ሪፖርቶችን አለማቅረብ፤

ተ) መዝገቦችን አለመያዝ ወይም መረጃ አለማቅረብ፤

ቸ) ትክክለኛ፣ የተሟላ ወይም ወቅታዊ መረጃ አለማቅረብ፤

ነ) የባለቤትነት ጣሪያዎችን ለማለፍ እና በርካታ ሂሳቦችን መጠቀም፤

አ) የጥንቃቄ ተጋላጭነት ገደቦችን መጣስ፤ ወይም

ከ) የሚያስፈልጉትን የካፒታል ወይም የገንዘብ ፍሰት መጠባበቂያዎች አለመያዝ (ለአገልግሎት ሰጪዎች)።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም፣ የዚህን ደንብ ማንኛውንም ድንጋጌ መጣስ በባለሥልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃ ያስከትላል።

፫/ ተፈጻሚነት ያላቸው ሌሎች የተከለከሉ ተግባራት እና አስተዳደራዊ እርምጃዎች ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናሉ።

## ክፍል አስራ ሁለት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፶፪. መመሪያ ስለማውጣት**

ባለሥልጣኑ ይህንን ደንብ በአግባቡ ለመተግበር እና ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

**፶፫. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ፣ መመሪያ፣ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

**፶፬. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

(ለህዝብ ምክክር የቀረበ ረቂቅ)

አዲስ አበባ _____ ቀን _____ ፪ሺ፲፱ ዓ.ም

**አብይ አህመድ አሊ (ዶ/ር)**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ጠቅላይ ሚኒስትር**

# ሰንጠረዥ "ሀ"

## ለውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተሮች የሚያስፈልጉ የብቁና ተገቢነት መስፈርቶች

### ፩. አጠቃላይ ግዴታዎች

| መስፈርት | ዝርዝር መግለጫ |
|---|---|
| 1.1. | እንደ የውጭ ፖርትፎሊዮ ኢንቨስተር ለመመዝገብ የሚያመለክት አመልካች፣ በመቀናጀት የሚንቀሳቀስ ማንኛውንም ሰው፣ ተጠቃሚ ባለቤቶችን፣ ዳይሬክተሮችን፣ ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎችን እና ፊራሚ ተወካዮችን ጨምሮ፣ በዚህ ሰንጠረዥ የተቀመጡትን የብቁና ተገቢነት መስፈርቶች በማንኛውም ጊዜ ማሟላት አለበት፡፡ |
| 1.2. | በዚህ ሰንጠረዥ የተቀመጠውን ማንኛውንም መስፈርት አለማሟላት ምዝገባን ለመከልከል፣ ውድቅ ለማድረግ፣ ለማገድ ወይም ለመሰረዝ ምክንያት ይሆናል፡፡ |

### ፪. ታማኝነት፣ ሐቀኝነት እና መልካም ስም

| መስፈርት | መግለጫ | ማረጋገጫ እና ሰነድ |
|---|---|---|
| 2.1. | አመልካቹ እና ቁልፍ ሰዎቹ ወይም በመቀናጀት የሚንቀሳቀሱ ሰዎች በማንኛውም ሀገር በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ በማቅረብ፣ ሽብርተኝነትን በገንዘብ በመርዳት ወይም በዓለም አቀፍ ስምምነቶች በተሸፈነ ሌላ ማንኛውም ዓይነት የተደራጀ ወንጀልን በገንዘብ መርዳት፣ ገበያን ያለ አግባብ መጠቀም፣ የውስጥ አዋቂ ግብይት ማካሄድ፣ ሐሰተኛ መረጃ መስጠት ወይም ሌሎች ከባድ ኢኮኖሚያዊ ወይም የፋይናንስ ወንጀሎች እና ጥፋቶች፣ የህዝብ ባለስልጣንን ጉቦ መስጠትን ወይም በህዝብ ባለስልጣን የሚፈጸም ማስገደድን ጨምሮ፣ ስርቆት፣ በማስፈራራት ገንዘብ መቀበል፣ ምዝበራ ወይም የእምነት ማጉደል፣ ማጭበርበር ወይም የተሰረቀ ንብረት መያዝ፣ በማጭበርበር የሚፈጸም መከሰር፣ የዘር ማጥፋት ወንጀል፣ በሰብአዊነት ላይ የሚፈጸም ወንጀል ወይም የጦር ወንጀል ተከሰው ጥፋተኛ ተብለው መገኘት የለባቸውም፡፡ | የወንጀል ሪኮርድ እና የቁጥጥር እርምጃ መግለጫዎች፡፡ |
| 2.2. | አመልካቹ በኢትዮጵያ ሕግ፣ በተባበሩት መንግስታት የጸጥታው ምክር ቤት ውሳኔዎች ወይም በሌሎች ተፈጻሚ ዓለም አቀፍ የማዕቀብ ስርዓቶች መሠረት ማዕቀብ የተጣለበት መሆን የለበትም፡፡ | የማዕቀብ ማጣሪያ ውጤቶች፡፡ |
| 2.3. | አመልካቹ እና ከአመልካቹ ጋር በመቀናጀት የሚንቀሳቀሱ ቁልፍ ሰዎቹ በባለሥልጣኑ እምነት በኢትዮጵያ ካፒታል ገበያ ውስጥ የመሳተፍ ብቁነታቸውን በወሳኝ ሁኔታ የሚያዳክም በሂደት ላይ ያለ የወንጀል ክስ ወይም ምርመራ ውስጥ መሆን የለባቸውም፡፡ | ለቁጥጥር የጀርባ ምርመራ የተሰጠ የጽሁፍ ፈቃድ፡፡ |
| 2.4. | አመልካቹ በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ተቆጣጣሪ፣ በፋይናንስ ተቆጣጣሪ ወይም ዕውቅና ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ የእገዳ፣ የክልከላ፣ የመከልከል ወይም ተመሳሳይ የማስፈጸሚያ እርምጃ ስር መሆን የለበትም፤ እንዲሁም ባለፉት አምስት (፭) ዓመታት ወይም ባለሥልጣኑ በሚደነግገው ሌላ ጊዜ ውስጥ ከባድ የቁጥጥር ጥሰቶች መዝገብ ሊኖረው አይገባም፡፡ | የቁጥጥር ማስፈጸም እርምጃ ታሪክ መግለጫዎች፡፡ |
| **፫. የፋይናንስ ጤናማነት** | | |
| **መስፈርት** | መግለጫ | ማረጋገጫ እና ሰነድ |
| 3.1. | አመልካቹ እና ከአመልካቹ ጋር በመቀናጀት የሚንቀሳቀሱ ሰዎች በማንኛውም ሀገር ውስጥ እዳቸውን መክፈል የማይችሉ፣ በኪሳራ ውስጥ ያሉ፣ በሃብት ማጣራት ሂደት ውስጥ ያሉ ወይም አቻ በሆነ ሂደት ውስጥ ያሉ መሆን የለባቸውም፡፡ | ኪሳራ ወይም ተመሳሳይ ሂደት አለመኖሩን የሚገልጽ ማረጋገጫ፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 3.2. | አመልካቹ ሊያከናውን ካሰበው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ባህሪ፣ መጠን እና የስጋት ገጽታ ጋር የሚመጣጠን የፋይናንስ አቅም ማሳየት አለበት፡፡ | የቅርብ ጊዜ የተመረመረ የሂሳብ መግለጫ፡፡ |

## ፬. ደንበኛን ማወቅ፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን መከላከል እንዲሁም የተጠቃሚ ባለቤትነት

| መስፈርት | መግለጫ | የሚያስፈልግ ሰነድ |
|---|---|---|
| 4.1. | አመልካቹ በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን ለመከላከል በወጡ የኢትዮጵያ ሕጎች እና ተፈጻሚ መመሪያዎች መሠረት የደንበኛ የተገቢነት ቁመና ጥናት፣ አስፈላጊ ሲሆንም የተጠናከረ ምርመራ ሊደረግበት ይገባል፡፡ | በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረትን ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን እና ሽብርተኝነትን በገንዘብ መርዳትን የመከላከል ምርመራዎች መጠናቀቃቸውን የሚገልጽ የጠባቂ ማረጋገጫ፡፡ |
| 4.2. | አመልካቹ የተሟላ እና ትክክለኛ የተጠቃሚ ባለቤትነት መረጃ ይፋ ማድረግ አለበት፡፡ | የተጠቃሚ ባለቤት መግለጫዎች እና የባለቤትነት መዋቅር ሰነዶች፡፡ |
| 4.3. | አመልካቹ የኢንቨስትመንት ካፒታሉን ሕጋዊ ምንጭ ለማረጋገጥ በቂ የሆነ የተረጋገጠ የገንዘብ ምንጭ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ | የገንዘብ ምንጭ ማስረጃ፡፡ |
| 4.4. | ለፖለቲካ ተጽዕኖ የተጋለጡ ሰዎች መለየት እና የተጠናከረ የተገቢነት ቁመና ጥናት ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ | ለፖለቲካ ተጽዕኖ የተጋለጡ ሰዎች ማጣሪያ ውጤቶች፡፡ |
| 4.5. | በቂ የስጋት የመቀነሻ ቁጥጥሮች ባለሥልጣኑን በሚያረካ ሁኔታ መኖራቸው ካልተረጋገጠ በስተቀር አመልካቹ ከፍተኛ ስጋት ያለው ወይም የማይተባበር ተብሎ በተለየ ሀገር ውስጥ ነዋሪ፣ የተመዘገበ ወይም በተግባር የሚመራ መሆን የለበትም፡፡ | የተረጋገጡ የማንነት እና የመቋቋሚያ ሰነዶች፡፡ |

## ፭. የውጭ ምንዛሪ እና የገንዘብ ምንጭ ሕግ ተገዥነት

| መስፈርት | መግለጫ | የሚያስፈልግ ሰነድ |
|---|---|---|
| 5.1. | ሁሉም የፖርትፎሊዮ ኢንቨስትመንቶች ከኢትዮጵያ ውጭ በተላለፈ ብቁ የውጭ ሀገር ገንዘብ ብቻ መሸፈን አለባቸው፡፡ | ፈቃድ ያለው የባንክ ሂሳብ ሰነድ፡፡ |
| 5.2. | በውጭ ምንዛሪ የሚፈጸሙ ሁሉም ግብይቶች፣ ልውውጦች እንዲሁም ካፒታልን፣ የትርፍ ድርሻን፣ ወለድን እና ጥቅሞችን ወደ ውጭ ሀገር ማዛወር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመዝገብ እና በብሔራዊ ባንክ በተቀመጡት መስፈርቶቹ መሠረት መከናወን አለባቸው፡፡ | የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሪፖርት አቀራረብ ዝግጅት፡፡ |
| 5.3. | ሁሉም የውጭ ሀገር ገንዘብ ዝውውሮች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በተሰጣቸው ባንኮች በኩል መተላለፍ አለባቸው፡፡ | |
| 5.4. | አመልካቹ እና የተሰየመው ጠባቂ ሁሉንም የውጭ ምንዛሪ ሪፖርት አቀራረብ፣ ክትትል እና የመዝገብ አያያዝ ግዴታዎች ማሟላት አለባቸው፡፡ | |

## ፮. የአሰራር እና የገበያ ተደራሽነት መስፈርቶች

| መስፈርት | መግለጫ | የሚያስፈልግ ሰነድ |
|---|---|---|
| 6.1. | አመልካቹ የኢንቨስትመንት ተግባራትን ከመጀመሩ በፊት የኢትዮጵያ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማግኘት አለበት፡፡ | የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ምዝገባ የምስክር ወረቀት፡፡ |
| 6.2. | የኢንቨስትመንት ማመልከቻው በተሰየመው ጠባቂ ከጸደቀ በኋላ የተሾመው ጠባቂ ተፈጻሚ የሆኑትን የኢንቨስትመንት ጣሪያዎች | የጥበቃ እና የሂሳብ መክፈቻ ማረጋገጫዎች፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| | በማክበር የሚያስፈልጉትን የጥቢቃ፣ የጥሬ ገንዘብ፣ የውጭ ምንዛሪ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሳቦች መክፈት አለበት፡፡ | |
| 6.3. | የጥቢቃ፣ የሀብት መለያየት፣ የሪፖርት አቀራረብ እና የቁጥጥር ሕግ ተገዢነት ኃላፊነቶችን በግልጽ የሚያከፋፍል የጥቢቃ ስምምነት ከተሰየመው ጠባቂ ጋር መፈረም አለበት፤ ስምምነቱም በአምስት (፭) የስራ ቀናት ውስጥ ለባለሥልጣኑ ሪፖርት መደረግ አለበት፡፡ | የጠባቂነት ውል እና የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሂሳብ መዝገቦች፡፡ |

## ፯. ተጨማሪ ሰነዶች (እንደ አግባብነቱ)

| **መስፈርት** | **መግለጫ** | **የሚያስፈልግ ሰነድ** |
|---|---|---|
| 7.1. | አመልካቹ በሚገኝበት ሀገር በሚመለከተው አካል የተሰጠ የጸና የግብር ነዋሪነት የምስክር ወረቀት ወይም አቻ ሰነድ ማቅረብ አለበት፡፡ | የግብር ነዋሪነት የምስክር ወረቀት ወይም አቻ ሰነድ፡፡ |
| 7.2. | አመልካቹ የተረጋገጡ የመቋቋሚያ ሰነዶችን እና የተቋሙን መገለጫ ማቅረብ አለበት፡፡ | የመቋቋሚያ ሰነዶች እና የተቋም መገለጫ፡፡ |
| 7.3. | አመልካቹ የቦርድ አባላቱን እና የከፍተኛ የስራ ኃላፊዎቹን ዝርዝር ማቅረብ አለበት፡፡ | የቦርድ አባላት እና የከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ዝርዝር፡፡ |
| 7.4. | ተቋማዊ ኢንቨስተሮች በኢትዮጵያ ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ላይ ኢንቨስት ለማድረግ የሚፈቅድ የቦርድ ውሳኔ ማቅረብ አለባቸው፡ ፡ | በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ የተላለፈ የቦርድ ውሳኔ፡፡ |
| 7.5. | ቁጥጥር የሚደረግባቸው ተቋማት ከሚገኙበት ሀገር ተቆጣጣሪ የተሰጠ ፈቃድ፣ የፈቃድ ማረጋገጫ ወይም የማረጋገጫ ደብዳቤ ማቅረብ አለባቸው፡፡ | ከሚገኙበት ሀገር ተቆጣጣሪ የተሰጠ ፈቃድ ወይም የማረጋገጫ ደብዳቤ፡፡ |
| 7.6. | እንደ አግባብነቱ፤ አመልካቹ ከሚገኝበት ሀገር ተቆጣጣሪ የዓለም አቀፉ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኮሚሽኖች ድርጅት (IOSCO) የብዝሃ ወገን የመግባቢያ ሰነድ ፈራሚ መሆኑን ወይም ከባለሥልጣኑ ጋር አቻ የሆነ የትብብር ዝግጅት መኖሩን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፡፡ | የዓለም አቀፉ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኮሚሽኖች ድርጅት የብዝሃ ወገን የመግባቢያ ሰነድ ፈራሚነት ወይም የትብብር ዝግጅት ማስረጃ፡፡ |

## ፰. የሰነድ መመዘኛዎች (አስገዳጅ)

| **መስፈርት** | **መግለጫ** |
|---|---|
| 8.1. | በዚህ ሰንጠረዥ መሠረት የሚቀርቡ ሁሉም ሰነዶች በሙሉ ስልጣን ባለው የሰነዶች አረጋጋጭ አካል የተረጋገጡ ቅጂዎች መሆን አለባቸው፡፡ |
| 8.2. | በእንግሊዝኛ ያልተዘጋጀ ማንኛውም ሰነድ ወደ እንግሊዝኛ ወይም ወደ አማርኛ ከተተረጎመ የተረጋገጠ ትርጉም ቅጅ ጋር አብሮ መቅረብ አለበት፡፡ |